



# ድሬ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 865 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | የካቲት / 27 / 2016 ዓ.ም



## ይፍጠኑ!

እስከ የካቲት 30/2016 ዓ.ም ድረስ ብቻ የሚቆየውን የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን የአባላት ምዝገባና ዕድሳት ያከናዉኑ፡፡

የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሁኑ!

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ


# የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር እና ካቢኔያቸው በአዲስ አበባ የተገነቡ ህብረተሰብ ተኮር የልማት ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን የሆኑ ፕሮጀክቶች የሚደነቁ በመሆናቸዉ፥ በድሬዳዋ አስተዳደር በሰው ተኮር ስራዎች የሚተገበሩ እንደሆነ ተገለፀ።

ቡድኑ ተዘዋውሮ ከጎበኛቸው የልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ ተስፋ ብርሀን የምገባ ፕሮግራም፥ የሴቶች ማበልፀጊያ ማዕከል እንዲሁም የለሚ የእንጀራ ማምረቻ ፋብሪካ ፣ የአረንጓዴ ልማትን እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ይገኙባቸዋል።

ካቢኔው በአጭር ግዜ ተሰርቶ የተጠናቀቀውን የአድዋ መታሰቢያ ሙዚየምን የጎበኘ ሲሆን፥ ከንቲባ ከድር ጁሀር ይህ ፕሮጀክት ቁርጠኝነት እና በሳል አመራር የታየበት ነው ሲሉ ገልፀዋል።

በጉብኝቱ እና ልምድ ልውውጡ የተገኙ ተሞክሮዎችንም በመቀመር የተመረጡ ፕሮጀክቶችን ወደ ተግባር እንደሚያስገቡም ከንቲባው ማስታወቃቸውን ድሬ ቲቪ ዘግቧል።



## በኢትዮጲያ የእንግሊዝ ኤምባሲ ከድሬዳዋ አስተዳደር ጋር በትብብር ሊሰሩ በሚያስችላቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄዱ




በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር ዳረን ዌልች ከድሬዳዋ አስተዳደር ከፍተኛ የመንግሥት ሀላፊዎች ጋር በትብብር ሊሰሩ በሚያስችላቸው ጉዳዮች ላይ ፍሬያማ ውይይት አካሂደዋል ።

አምባሳደሩ እንግሊዝ ከድሬዳዋ አስተዳደር ጋር ከዚህ በፊት በጀመረቻቸው እና በአዳዲስ የልማት እቅዶች ላይ በትብብር ለመሥራት ፍላጎት ያላት መሆኑን ተናግረዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሀላፊ ወ/ሮ ሙሉካ መሀመድ ከዚህ በፊት በንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በትምህርትና ስልጠና፣ በኢንቨስትመንት አማራጮች ዙሪያ ከአስተዳደሩ ጋር በትብብር እየሰሩ መሆኑን አንስተው በቀጣይ ድጋፋቸውን እንዲያጠናክሩም ጠይቀዋል።


ወደ ገጽ 10 ዞሯል


## 9ኛው የአፍሪካ የትምህርት ቤት ምገባ ቀን  በድሬዳዋ አስተዳደር ተካሄደ



በአፍሪካ ለዘጠነኛ ጊዜ በሀገራችን ኢትዮጲያ ደግሞ ለአምስተኛ ጊዜ “ ሀገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ መዋለ ንዋይን ማፍሰስ ለተሻለ ትውልድ ግንባታ “ በሚል መሪ ቃል የአፍሪካ የትምህርት ቤት ምገባ ቀን በክብር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ ስም በተሰየመው ገንደ ገበታ አንደኛና መካከለኛ ትምህርት ቤት ላይ ተካሂዷል ።

በዚሁ መርሀ-ግብር ላይ የተገኙት  የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሀር ለተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ እንደ ሀገር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ተናግረው በድሬዳዋ አስተዳደርም ይህንኑ የተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባን በመተግበር የወላጆችን ጫና መቀነስ ከመቻሉም በላይ ተማሪዎች ተረጋግተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ መቻሉን ነው ያስታወቁት።

የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብር በሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች አካባቢ ህብረተሰቡን በማስተባበር  የምግብ ማብሰያ ኩሽና እና የምግብ ማከማቻ መጋዘን ለመስራት ፣ ለምግብ አብሳይ ሰራተኞች


ወደ ገጽ 10 ዞሯል


## < <በተቋማት የሚታዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ከሰላም እጦት ተለይተው ሊታዩ አይገባም> >

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ሀርቢ ቡህ




የአስተዳደሩ የሪፎርም አስተግባሪ ቴክኒካል ኮሚቴ ከሰሞኑ በተቋማቱ ያለውን የትግበራ ደረጃ ለመገምገም ያደረገውን ሱፐርቪዥን በተመለከተ የተዘጋጀ ሪፖርት በድሬዳዋ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የሪፎርም ትግበራ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ባቹሬ በዝርዝር ለአብይ ኮሚቴው ቀርቦ ተገምግሟል፡፡

በአጠቃላይ በዝግጅት ምዕራፍ እስካሁን በተቋማቱ የነበረውን አፈፃፀም መነሻ በማድረግ የታዩ ጥንካሬዎች እና ውስንነቶች በዝርዝር በሪፖርቱ የተመላከቱ ሲሆን በቀጣይም በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተቀመጠውን የ3ኛው ትውልድ የተቋማት ሪፎርም የትግበራ አቅጣጫ መሰረት ባደረገ መልኩ የተዘጋጀው የአንድ ወር የዝግጅት ምዕራፍ የሪፎርም ስራዎች ማስፈፀሚያ የድርጊት መርሀ-ግብርም ለአብይ ኮሚቴው የቀረበ ሲሆን በአፈፃፀሙና የቀጣይ አካሄዶችን በተመለከተ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በመርሀ- ግብሩ መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን ሙሉበሙሉ


ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# በፍትህ ዘርፍ የማስፈጸም አቅምን በማሳደግ ለህብረተሰቡ ተደራሽነትና ተገማችነት ያለዉ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በትኩረት እየተሰራ መሆኑ ተገለፀ

በህዝብ ቅሬታ እና አቤቱታ አፈታት ላይ ያተኮረ ስልጠና በድሬደዋ ለሚገኙ ሁሉም የወረዳ እና ገጠር ክላስተር አመራሮች እና ባለሙያወዎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሴክተር ተቋማትን ለተውጣጡ ለለውጥና መልካም አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እና ለሰው ሀብት አመራሮች ስልጠና ተሰጠ ተሰጠ።

በስልጠናው መክፈቻ ላይ የድሬደዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ም/ኃላፊ ክብርት ወ/ሮ ሰአዳ አዋሌ እንደተናገሩት በከተማም ሆነ በገጠር በመንግስት የአገልጋይነት ቦታ ላይ ተቀምጠው ህዝብን እንዲያገለግሉ እድሉን ያገኙ አመራርም ሆነ ባለሙያዎች የህዝብን ፍላጎት ተረድተው ባግባቡ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲያገኝ መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። በተለይ በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያገለግሉ የወረዳ እና የገጠር ክላስተር አመራሮች ለአገልግሎት አሰጣጥ ተግዳሮት የሆኑ ቢሮክራሲዎችን እና ለመልካም አስተዳደር መንስኤ የሆኑ ችግሮችን አጥርተው በመለየት ለተሻለ ግልጋሎት እንዲሰሩ አሳስበዋል። በስልጠናው በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በተሻሻለው



የመልካም አስተዳደር መርሆች ትግበራ ላይ በሚቀርቡ ሰነዶች ላይ በመወያየት ግብአት ሊሆኑ ሚችሉ ሀሳቦች እንደሚቀርቡ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

ቅሬታዎች በጊዜ ካልተፈቱ አቤቱታውም ምላሽ ካላገኘ የህዝብ የመልካም አስተዳደር ችግር ስለሚሆኑ ሁሉም አመራርም ሆነ ባለሙያ ይህን በመረዳት ለችግሩ መፍትሄ ሚሆኑ አሰራሮችን መዘርጋት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ አሳስበዋል።

የእለቱ ስልጠናም አገልጋዩ ተገልጋይ አቤቱታ እና ቅሬታን ይዞ ሲቀርብ እንዴት ባጭር ጊዜ መፍታት እንደሚችል እና ህጉ በዚህ ረገድ ምን ይላል ሚለውን መነሻ ተደርጎ መሰጠቱን ነው የገለፁት። መድረኩ በድሬደዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/2014 ላይ ግንዛቤ ሚፈጥሩ ፅሁፎችና እንዴት በቀጣይ ተቀናጅቶ በመስራት የህዝብን እርካታ በመፍጠር ለህዝብ ቅሬታ መንስኤ የሆኑ ችግሮችን መፍታት ይቻላል በሚሉት ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። በመድረኩ ከከተማ ወረዳዎች እና ገጠር ክላስተር እንዲሁም ሚመለከታቸው ሴክተር ተቋማት አመራር እና ኃላፊዎች ተሳታፊ ሆነዋል ሲል የከንቲባ ጽ/ቤት የደረሰን መረጃ ያመላክታል፡፡

# የመንግስትና ህዝብን ውስን ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የፋይናንስ ባለሞያዎችና የተቋማት የውስጥ ኤዲተሮች ሙስናን በግንባር ቀደምትነት ሊዋጉ እንደሚገባ ተገለጸ

የድሬዳዋ አስተዳደር ስነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን በአስተዳደሩ ሴክተር መስሪያቤቶች ለሚገኙ የፋይናንስ ባለሞያዎችና የውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ሰጠ ፡፡

ሙስና የሀገር ውስን ሀብት ያላግባብ ባክኖ ልማት የሚደናቀፍበትና እድገት የሚቀነጭርበት ተግባር መሆኑን በመገንዘብ ፤ ሀገሬንና ህዝቤን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ ሊፀየፈው ይገባል ያሉት የድሬዳዋ አስተዳደር ስነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ፌኑስ አብዱልጀባር፤ በተለይም የመንግስት ተቋማት የውስጥ ኦዲተሮች እና የፋይናንስ ባለሞያዎች ሙስናን በመዋጋት ረገድ ያላቸውን አይተኬ ሚና በሙሉ ኃላፊነት እንዲወጡ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራ አካል ነው ስልጠናው ብለዋል ፡፡

የመንግስትና የህዝብን ሀብት ለታለመለት ዓላማ ይውል ዘንድ ትልቁ ሞያዊ ኃላፊነትና እምነት የተጣለው በፋይናንስ ባለሞያዎችና የውስጥ ኦዲተሮች ላይ እንደመሆኑ ፤ ይሔንን ኃላፊነታችንን በሙሉ አቅም




እንድንወጣና ችግሮችም ሲያጋጥሙ ከሚመለከተው የህግ አካል ጋር እንዴት በቅንጅት መስራት እንዳለብን ግንዛቤ የሰጠን ስልጠና ነው ያለው ሰልጣኝ የድሬዳዋ ድል ጮራ ሪፈራል ሆስፒታል የውስጥ ኦዲተር ነው ፡፡

ሙስና የሀገርና የህዝብ ሀብት እንዲመዘበር የሚያደርግና አፍራሽ የስነምግባር ጉድለት ብቻ ሳይሆን ተግባሩ ተፈጽሞ ሲገኝም ወንጀል መሆኑን ማወቅና ራስን ከዚህ ማራቅ ብሎም ተግባሩ እንዳይፈጸምም አስቀድሞ በመከላከል አኳያ የፋይናንስ ባለሞያዎች ድርሻችን የጎላ በመሆኑ ፤ ስልጠናው ትልቅ አቅም የሚፈጥርልን ነው ያሉት ደግሞ የድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የፋይናንስ ባለሞያ ናቸው፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር ስነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ፌኑስ አብደላ የፋይናንስ ባለሞያዎችና የውስጥ ኦዲተሮች ሳያውቁት በየትኛውም ተቋም ውስጥ የሚንቀሳቀስ ገንዘብ ሊኖር ስለማይችል የሙስና ተግባር እንዳይፈጸም አስቀድሞ በመከላከል በኩል የተጣለባቸውን ህዝባዊ አደራና ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ ይገባል ብለዋል ፡፡

**በዳንኤል አማረ**

**ፎቶ ፡- ሙሉዓለም ደሴ**

# በህዝብ ቅሬታ እና አቤቱታ አፈታት ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ

በከተማም ሆነ በገጠር በመንግስት የአገልጋይነት ቦታ ላይ ተቀምጠው ህዝብን እንዲያገለግሉ እድሉን ያገኙ አመራርም ሆነ ባለሙያዎች የህዝብን ፍላጎት ተረድተው ባግባቡ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲያገኝ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተገለፀ

በህዝብ ቅሬታ እና አቤቱታ አፈታት ላይ ያተኮረ ስልጠና በድሬደዋ ለሚገኙ ሁሉም የወረዳ እና ገጠር ክላስተር አመራሮች እና ባለሙያወዎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሴክተር ተቋማት ለተውጣጡ ለለውጥና መልካም አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እና ለሰው ሀብት አመራሮች ስልጠና ተሰጠ።

በስልጠናው መክፈቻ ላይ የድሬደዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ም/ኃላፊ ክብርት ወ/ሮ ሰአዳ አዋሌ እንደተናገሩት በከተማም ሆነ በገጠር በመንግስት የአገልጋይነት ቦታ ላይ ተቀምጠው ህዝብን እንዲያገለግሉ እድሉን ያገኙ አመራርም ሆነ ባለሙያዎች የህዝብን ፍላጎት ተረድተው ባግባቡ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲያገኝ መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። በተለይ በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያገለግሉ የወረዳ እና የገጠር ክላስተር አመራሮች ለአገልግሎት አሰጣጥ ተግዳሮት የሆኑ ቢሮክራሲዎችን እና ለመልካም አስተዳደር መንስኤ የሆኑ ችግሮችን አጥርተው በመለየት




ለተሻለ ግልጋሎት እንዲሰሩ አሳስበዋል። በስልጠናው በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በተሻሻለው የመልካም አስተዳደር መርሆች ትግበራ ላይ በሚቀርቡ ሰነዶች ላይ በመወያየት ግብአት ሊሆኑ ሚችሉ ሀሳቦች እንደሚቀርቡ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

ቅሬታዎች በጊዜ ካልተፈቱ አቤቱታውም ምላሽ ካላገኘ የህዝብ የመልካም አስተዳደር ችግር ስለሚሆኑ ሁሉም አመራርም ሆነ ባለሙያ ይህን በመረዳት ለችግሩ መፍትሄ ሚሆኑ አሰራሮችን መዘርጋት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ አሳስበዋል።

የእለቱ ስልጠናም አገልጋዩ ተገልጋይ አቤቱታ እና ቅሬታን ይዞ ሲቀርብ እንዴት ባጭር ጊዜ መፍታት እንደሚችል እና ህጉ በዚህ ረገድ ምን ይላል ሚለውን መነሻ ተደርጎ መሰጠቱን ነው የገለፁት። መድረኩ በድሬደዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/2014 ላይ ግንዛቤ ሚፈጥሩ ፅሁፎችና እንዴት በቀጣይ ተቀናጅቶ በመስራት የህዝብን እርካታ በመፍጠር ለህዝብ ቅሬታ መንስኤ የሆኑ ችግሮችን መፍታት ይቻላል በሚሉት ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። በመድረኩ ከከተማ ወረዳዎች እና ገጠር ክላስተር እንዲሁም ሚመለከታቸው ሴክተር ተቋማት አመራር እና ኃላፊዎች ተሳታፊ መሆናቸውን ነው ከድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው፡፡

# ርዕሰ - አንቀጽ

## እውነቱን ከጠላትህ ስማ

አንድ ንጉሥ አንድ ብልህ አጫዋች ነበራቸው። በየጊዜው ከሚመክራቸው ምክር መካከል ሰሞኑን የነገራቸውን ለመቀበል ከብዷቸዋል። ሰሞኑን የመከራቸው "ከወዳጆችዎ ይልቅ፣ ስለርስዎ ድክመት ዕውነቱን የሚነግሩዎ ጠላቶችዎ ናቸውና አዳምጧቸው" የሚል ነበር።

ንጉሡ አላመኑበትም። ስለዚህ ለማረጋገጥ መዘዋወር ጀመሩ። ንጉሡ በጣም የሚፈሩና አይበገሬ ነኝ የሚሉ ናቸው። በሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚያገኟቸውን መኳንንቶች "እስቲ ስለ እኔ ጉድለት ንገሩኝ?" ይሉና ይጠይቃሉ። "ንጉሥ ሆይ! እርስዎ ላይ እንዴት አይነት ሰው ነው ጉድለት ሊያገኝ የሚችለው። ደግሞ እርስዎ ምን ይወጣልዎታል!" ይሏቸዋል። ቀጥለው ወደ ሠራዊታቸው ይሄዱና፤"ምን እንከን አለብኝ? እስቲ ስለራሴ ንገሩኝ?" ይላሉ። ከሠራዊታቸው ታማኙ ባለሚል ብድግ ብሎ፣"ንጉሥ ሆይ! እርስዎ ከቁመናዎ ጀምሮ፣ ለጀግንነትዎ፣ ለዕውቀትዎ፣ ለዓለም ተደማጭነትዎ ምን የሚቀነስ የሚወጣልዎ ነገር አለብዎ!" ይላቸዋል።

እንዲህ ከርመው አንድ ቀን በአጋጣሚ ከጠላቶቻቸው ጋር በሚሲዮን ይቀመጣሉ። አጠገባቸው የተቀመጠው ቀንደኛው ባላንጣቸው ቀስ ብሎ፤ "ስሙ ንጉሥ፤ ሲናገሩ አፍዎት መጥፎ ጠረን ያመጣል" ይላቸዋል። ንጉሱ ይናደዳሉ። "እንዴት እስከዛሬ አንድ ወዳጄ ይሄን አልነገረኝም? እንዲህ በአደባባይ እንድጋለጥ ያደረጉኝ ወዳጆቼ ናቸው! ቆይ ግድ የለም! ባልሰራላቸው!" ይላሉ በሆዳቸው። ስብሰባውን እንደጨረሱ ሲገሰግሱ ወደ ቤተ-መንግስታቸው ይሄዱና ንግስቲቱን አስጠርተው፤"አፌ ጠረን እንዳለው እስከዛሬ ያልነገርሽኝ ለምንድን ነው?" ሲሉ በቁጣ ጠየቁ። ንግስቲቱም፤ በንፁህ ልቦናና በቀናነት፤ "ንጉሥ ሆይ! የሁሉም ንጉስ አፍ እንደ እርስዎ አፍ አይነት ሽታ ያለው መስሎኝ ነው" ሲሉ መለሱ።

ንጉሡም እጅግ የቅርባቸው የሆነችው የገዛ ባለቤታቸው ጉድለታቸውን ሳትነግራቸው፤ ሩቅ የሚኖሩት ጠላቶቻቸው ማወቃቸውን ልብ ሲሉ፤ ያ አስተዋይ አጫዋቻቸው የነገራቸው ቁም ነገር እውነት መሆኑን ተገነዘቡ።

ማንኛውም መሪ፣ በማንኛውም ደረጃ ያለ ቢሆን፤ አንድ ሀቅ ልብ ማለት አለበት። ራሱን ብቻ የሚያዳምጥ መሪ፤ ከወዳጆቹ የሚጠብቀው ምንጊዜም ምስጋናን ስለሆነ ጉድለቶቹን የማየትም የመስማትም እድል አያገኝም። ወገኖቹም አይደፍሩትም። እሱም ራሱን አይደፍርም። ይህ ሁሉ የሚሆነው ሁሌ በሰላም ጊዜ በሆነ ባልከፋ። ሁኔታዎች በውጥረትና በችግር በሚሞሉበት ሰዓት ሲመጣ ነው አደጋው። ምክንያቱም የሁኔታዎች መወሳሰብን ተከትለው ሰዎችም ይለወጣሉና ነው። ችግሩ ግን በዚህ ብቻ አያቆምም። መሪውን መስለውና አክለው ማደግ ሲሞኙ የቆዩ ባለሚሎቹና ተከታዮቹ አለማዳመጥ ሰናይ ስነምግባር እየመሰላቸው እነሱም እኩዮቻቸው የሚሉትን አልሰማ ይላሉ። በዚህ ምክንያት ካለመደማመጥ አልፎ፣ የሚፈጠረውን ጩኸት ለመገደብ ካለመቻል ደረጃ ይደረሳል። በየመንበራቸው እንደተቀመጡ በየራሳቸው ደሴት ውስጥ ይዋጣሉ። ውለው አድረውም የታችኞቹ በላይኞቹ ላይ ቅያሜን ያጠነክራሉ። ቀስ በቀስ በተለይ የመረረ የመከፋት ስሜት ውስጥ በገቡ ጊዜ፤ እንደ ሮማው ካሽየስ፣ ባለቃው ላይ ማሴርን፣ ራስን እንደማዳን ሲቆጥሩ፤ ከላይ ወደ ታች ይወርዱ የነበሩ ትእዛዛት ወደ ጎንም፣ ወደ ላይም እንዲያመሩ ሲፈለግ፣ ለወትሮው የአለቃውን ድክመት ሁሉ የእኔ ነው እያለ አሜን ይል የነበረው ሁሉ፣ ድርሻ ድርሻችንን እንውሰድ በሚል፤ ሌላውን ማነሳሳትና ብሶቱን ሌላው ላይ ማጋበቱን ይያያዘዋል። ይሄኔ እንደ ሮማው ብሩተስ ያለው በትዕግስት የሚያገኘውን ስልጣን ቄሳርን በማስወገድ ሊፈጽመው እንዲሻ ሲተነኮስ፣ ወይም ሲወነባበድ፣ ነገር የተገላቢጦሽ ይሆናል። ቄሳር በመሞቻው "አንተም ብሩተስ?" ያለበት ሰዓት የሚመጣ እንግዲህ ያኔ ነው።

የሚያግባባንን መንገድ ከንፍቀ-ክበባችን ውጭም ቢሆን ማዳመጥ፣ ከባላንጣዎቻችንም ቢሆን መማር፣ ሁሌ ከመተላለፍ አንዳንዴ "ምን ይሆን?" ብሎ ለሌሎች ሀሳብ ትንሽ እድሜ መለገስ፤ ቀስ በቀስ ግትርነታችንን ሊያረግበው ይችላል።

አለንልህ ያልነውንና በእርሱም ትከሻ ለስልጣን የበቃንለትን፣ ከቀን በኋላ ከእርሱ እጅ የማንወጣውን ህዝብ ማዳመጥ እንደሚኖርብን እንድናስብም ፋታ ይኖረናል።

ስለሌላው ውሸት እንጂ እውነት በተናገርን ቁጥር፣ ስለሌላው ድክመት እንጂ አንድ አንኳር ጥንካሬ እንኳን ባነሳን ቁጥር፣ እኛ ብቻ ሀቀኛ፣ እኛ ብቻ ጠንካራ እያልን እንገበዛለን። ይህ ደግሞ ስለራሳችን እውነተኛ ገጽታ እንዳናውቅ ያደርገናል። የእኛኑ ቅኝት የሚያዳምጡ ወገኖቻችንና ደጋፊዎቻችን እውነተኛ ይዘትና ቅርጻችንን አይነግሩንም።

ስለዚህ ከእኛ ውጭ የማዳመጥ ባህል ማዳበር ደግ ነገር ነው- ከ"ጥላትም" ሰፈር ቢሆን። አበው "ከፋትህና ውሸትህ ሲጠፋብህ፤ ጠላትህን አስታውሰኝ በለው" የሚሉት ይሄንኑ ሊያስገነዝቡን ነው፡፡

# አጀንዳ

## "የህጻናት አስም"

በዶ/ር ንጉሤ ጫኔ :

የህጻናት ስፔሻሊስት ሀኪም

- አስም ምንድን ነው?

አስም የመተንፈሻ አካላችን ባእድ በሆኑ የትንፋሽ አለርጅ ቀስቃሽ ኬሚካሎች ተጽእኖ ከሚገባው በላይ በድንገት ለተወሰነ ጊዜ መጥበብ ነው። ይህ የአየር ቧንቧ ጥበት መድሀኒት ሲዎስዱ ወደ ነበረበት በቀላሉ ሊስተካከል የሚችል ነው።

- ምክንያተ መንስኤ

ዋና ምክንያቱ ተፈጥሯዊ ፣ከባቢያዊ እና ቀስቃሽ በሆኑ ምክንያቶች ይነሳል። የሚፈጠረው መስተጋብር አየር ባንቧን ለዘለቀ ቁስለት/ብግነት በማጋለጥ አለርጅ ቀስቃሽ ሽታዎች ሲኖሩ የአየር ቧንቧ ከልክ ያለፈ ተለዋጭ ጥበት እና የቆሸሸ አየር ከሳንባ በሚፈለገው ልክ አለመውጣት ሳል እና የመታፈን ምክንያትን ያመጣል። ከባቢያዊ እና ቀስቃሽ ምክንያቶችን መቀነስ ይቻላል።

- የአስም አይነቶች

1. በተደጋጋሚ የሚነሳ አስም/recurrent asthma/ seasonal

ይህ ወቅታዊ ሁኔታዎች የሚያስነሱት አስም ነው። ቀስቃሽ ምክንያቶችን በመቀነስ ድግግሞሹን መቀነስ እና ደረጃውንም መቆጣጠር ይቻላል።

2. ረጅም ጊዜ የቆየ አስም /chronic asthma

ለረጅም ጊዜ የዘለቀ አስም

- አለርጅ/አስም ቀስቃሾች ምንድን ናቸው?

1. የሲጋራ ፣ የከሰል እና የማገዶ ጭስ

2. የአበባ፣ቆሻሻ፣ የፅዳት መጠበቂያ/ዴቶል/ ፣ የሽቶ እና ላበት ማጥፊያዎች ሽታ

3. ላባ እና ጸጉር ያላቸው የቤት እንስሳት

4. የከብቶች ሽንት እና አዛባ

5. በረሮ የሚረጨው ኬሚካል

6. እርጥበት እና ቅዝቃዜ ያለው ስፍራ

7. የጉንፋን ቫይረስ

8. የኬሚካል ሽታ

9. ጭንቀት እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ

10. ሻጋታ

11. የጨጓራ አሲድ ቅርሻ/Gastro esophageal reflux disease

12. የአፍንጫ አለርጅ እና ሳይነስ ህመም

- ለአስም አጋላጭ ሁኔታዎች

1. የቆዳ አለርጅ/የቆዳ አስም

2. የአፍንጫ እና አይን አለርጅ

3. የምግብ አለርጅ

4. አስም ያለበት እናት ፣ አባት ፣ እህት ወይም ወንድም

5. ከጉንፋን ጋር የማይያየያዝ ሳል

- የህመም ምልክቶች

1. በቅዝቃዜ ወቅት እና ማታ ማታ የሚባባስ ደረቅ ሳል

2. የደረት መጨነቅ/የመታፈን ስሜት

3. የትንፋሽ መፍጠን

4. የድካም ስሜት

5. የሰውነት መዛል እና ላበት

6. ሙዚቃዊ ትንፋሽ

7. ራስ ምታት፣ የትኩረት መቀነስ፣ እና አቅልን መሳት

- አስም አመላካች ነገሮች ምን ናቸዉ

1. በጥርጣሬ የአስም መድኃኒት ሲሰጥ በቶሎ የሚሻል ከሆነ

2. ወላጅ አስም ወይም አለርጅ ካለበት

3.ነባር የትንፋሽ አለርጅ ካለ

4. ተደጋጋሚ የመተንፈሻ አለርጅ:

- ህጻናት ላይ አስም የምንለው በአመት ውስጥ ሶስት ጊዜ እና ከዚያ በላይ የሆነ ሀኪም ያረጋገጠው የመተንፈሻ አለርጅ ካለ ነው።

- አስምን በምን እናረገግጣለን

1. የሳንባ ምርመራ:

በጤንነታቸው ወቅት ያላቸው የሳንባ አየር የማስገባት እና የማስወጣት የመጨረሻ አቅም ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል በህመሙ ምክንያት ቀነሰ የሚለውን በመለካት።

2. የአየር ቧንቧ ለትንፋሽ ቧንቧ አስፊ ህይዎት አድን መድሀኒት ያለውን ፈጣን ምላሽ በማየት።

3. በአለርጅ አምጭ/ቀስቃሽ መድሃኒት አስም የመከሰት እድሉን መሞከር(ይህ ምርመራ ብዙ አይመከርም)

4. በስፓርታዊ እንቅስቃሴ ያለውን የተቃጠለ አየር የማስውጣት አቅም በመለካት።

- የአስም ህክምና

1. የአየር ቧንቧን ጥበት የሚያስተካክሉ መድሀኒቶች

2. የአየር ቧንቧ ቁስለትን/ብግነትን የሚቀንስ መድሃኒት

3. አለርጅን የሚቀንስ መድሃኒት

4. አስም ቀስቃሽ የሆነውን ህመም ማከም

5. ቤትን ከአስም ቀስቃሽ የሆኑ ነገሮች ነጻ በማድረግ አስም እንዳይነሳ መከላከል

6. በቅዝቃዜ እና ጉንፋን በሚበዛባቸው ወቅቶች የአስም ቅድመ መከላከል መድሃኒት መስጠት

የህጻናት የመተንፈሻ ቱቦ በተፈጥሮ ጠባብ በመሆኑ ምክንያት አስም ጋር የሚመሳሰሉ ብዙ ህመሞች ስላሉ አስም አለ የምንለው በታፈኑ ወቅት በአስም መድሀኒት ያላቸው ለውጥ አመርቂ ከሆነ እና ለአስም ተጋላጭነት ካላቸው ነው።

እድሜያቸው ከ4 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት የሳንባን በአግባቡ መስራት ወይም አለመስራት ለማወቅ ለምርመራ እድሜያቸው ስለማይፈቅድ በብዛት በክትትል ብቻ ነው መለየት የሚቻለው። አካባቢያዊ አስም ቀስቃሽ ሁኔታዎችን በማስተካከል አስምን መከላከል ዉጤታማ ነው።

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ -የካቲት / 27 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በድሉ ኃይሌ
ማቲያስ አንዳለ
እስከንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
አለም አስጨናቂ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ከፋይ ማነው?

## በስንታየሁ እንግዳ

ከፋይ ማነው?

ለባከነው ዘመን ለባከነው ጊዜ

ቸልታ ተጭኖን ይዞን ድንዛዜ

ማነው ተጠያቂ ማነው የሚቀጣ

እኔ ለክፈል የሚል እስቲ እጁን ያውጣ፡፡

ስንታየሁ 02/01/2013

የማህበራዊ የአኗኗር ዝብርቅርቅነት መምጫ ሰበቡ ብዙ ነው፡፡ መነሻው አንድም በያንዳንዳችን ቤት ያለው የአኗኗር ዘይቤ ለማህበረሰባዊ የአኗኗር ዝብርቅርቅነት ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡ ‹‹እያንዳንዱ ቤቱን ቢያፀዳ ፓሪስ ትፀዳለች›› እንደተባለው ማለት ነው፡፡ በርግጥ የእያንዳንዱ ቤት ፅዳ ማለት ፓሪስ ፅዳች ማለትም እንዳልሆነ ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ ምክኒያቱም ሁሉም ቤቱን አፅድቶ ቆሻሻውን በፓሪስ ጎዳናዎች ላይ ከጣለ እንዴት ሆና ፓሪስ ልትፀዳ ወዳጄ? ይልቁኑ ፓሪስ በራስ ወዳዶች ቆሻሻ ተበከለች ማለት እንጂ፡፡

እያንዳንዱ ፓሪሳዊ ነዋሪ ግን የቤቱን ቆሻሻ ከቤቱ አውጥቶ በሚገባው ስፍራ በመጣሉ ለፓሪስ የተነገረላት እውን ሆኖ ፅዱ ፓሪስን ማየት ተችሏል፡፡ እንደው ጉዳዩ ከነገሬ ጋር ገጥሞ ቀልቤን ቢስበው እንጂ ዛሬ እንድናወጋ የፈለኩት ስለ ፅዳት አይደለም ግን ደግሞ ጠለቅ ብለን ጉዳዩን ያየነው ከሆነ ርዕሰ ጉዳዬ የአንድ ሀገር ማህበረሰባዊ ንፅህና የሚጀምረው ከግለሰብ የማንነት ስነ-ልቦናዊ ንፅህና መሆኑን ስለሚታኝ አንዱ ለአንዱ ተመጋጋቢ ናቸው፡፡

የተተራመሰ ሀገር ካያችሁ መጠኑ ይብዛም ይነስ የተተራመሰ ቤተሰብ ነበረ ወይም አለ ማለት ነው፡፡ ለአንድ ሀገር/ማህበረሰብ መገኘት ቤተሰብ መነሻ ነጥቡ ነው፡፡ ለአንድ ሀገር በችግር አረንቋ መዘፈቅም በአንድም በሌላ በተፈጥሮ ችግር አሊያም ከውጭ ባለ ግፊት ካልሆነ በቀር መነሻው ቤተሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ የሚሆን አንድ ነጥብ እናንሳና እናወጋ፡፡ በሙስና አይደለም ስጋዋ የጀርባ አጥንቷ ሳይቀር የተጋጠችን ሀገር የጋጧትን ጋጠወጦች ያስተዳደግ ዘይቤ የቃኘን እንደሆን መነሻቸው ቤተሰብ ነው፡፡

‹‹እንዲህ ካደረክ እንዲህ አደርግልሃለሁ›› እንጂ ይሄን የምታደርው የማድረግ ግዴታ ወይም ኃላፊነት ስላለብህ ነው የሚል ቀና መንገድን ካለማስተማር የተነሳ የትናንቱ አበባዎች ዛሬ ፍሬ አፍርተው ሲያድጉ መንገዳቸው ያው ያደጉበት ይሆንና ዛሬም ባስቀመጥናቸው ስፍራ ሁሉን በገንዘብ ሊሸጡልን ይዳዳቸዋል ደግሞም ሲያደርጉትም ይስተዋላሉ፡፡ እጃቸውን ይዘን ያስተማርናቸው ትንንሽ ሙስና ትናንት እኛ የያዝነው እጅ ዛሬ የኛን እጅ ጠምዞ ሙስና ይቀበለናላ፡፡ ታዲያ ለዚህ በከንቱ ለባከነ የልጅነት ዕድሜ፣ ለዚህ በወጉ ሊመራ ሲገባው በተጣመመ መንገድ ተምዘግዝጎ ላደገ ማንነት ያባከነውን ጊዜ ከፋዩ ማነው?

በልጅነቱ ዘመን ‹‹ሊበላብህ ነው ቶሎ ቶሎ ብላበት›› ተብሎ ያደገ ጎልማሳ አሊያም ብቻውን ያለሰው የሚኖር ያክል ከሌሎች ልጆች ተነጥሎ አንተ እኮ ልዩ ነህ እየተባለ ያደገ ሰው ሙሉ በሙሉ ሳፋ የሚክል ምግብ የሞላው ትሪ/ሳህን ለብቻው እንደ ሀገር ነፃ አውጪ ተቆጣጥሮ ይዞ በዙሪያው ሌላ የተራበ ሰው የሌለ ያክል ሲያሻምድ ላስተዋለ ይሄን ሰው ምን አስቦ ምን ስያሜ ሊያወጣለት ይሆን? እኔ በበኩሌ ምንም የምሰጠው ስያሜ የለም ምክኒያቱም ግለኝነትን በጠዋቱ አስተምረውት ዛሬ ለዚህ ክፉ ዓመል የዳረጉትን ወላጅ አሳዳጊዎቹን ዛሬ ያኔ ያበላሻችሁበትን ፈጣሪ የሰጠውን የማካፈል ፀጋ ወደ ነበረበት ለመመለስ የባከነውን ያን ጊዜ የሚከፍለው ማን ይሆን ከማለት ወዲያ፡፡

ገና በጨቅላነት ሀገራዊ ፍቅርን በተረት፣ በትምህርት፣ በጨዋታ፣ በእንቆቅልሽ ወዘተ. በልብ ጥልቀት ማስገባትና ከማንነታችን ጋር ማዋሃድ ሲገባ ከእኛነት ይልቅ እኔነትን ብቻ በልጅነት አዕምሮው ጠቅጥቀንበት ዛሬ ይዞት ላደገው እኛ ትልቅ ከማለት ይልቅ ‹‹እኔ ብቻ ትልቅ›› ወደሚል መስመር አጋድሎ እርስ በእርስ የሚያገዳድል ደረጃ ላይ ላደረስነው ትውልድ ተጠያቂው አሊያም ለዛ ለግለኛ ሰው ለባከነበት የልጅነት ዘመን ከፋይ ማን ይሆን?

አሁንስ ቢሆን አንደሚጋለብ የጠገበ ፈረስ የስልጣን እርካብን ከተቆናጠጡ በኋላ ቀድመው ሳር ነጭቶ ድንጋይ ተሸክሞ የመማል ያክል በየሚዲያውና በየ ስብሰባ አዳራሹ ነብሴ እስክትወጣ ሳልበላና ሳልጠጣ እንቅፋት ሲመታህ እኔ ቀድሜ ልወድቅልህ ዝግጁ ነኝ ያሉትን ሕዝብ እንደተሾሙ የሙከራ ስርጭት ይመስል ሮጥ ሮጥ ይሉለትና ወይ ሊጀምሩ ያሰቡን አሊያም ያስጀመሩትን እንኳን ዳር ሳያደርሱ የተቀመጡበት ወንበር ሞቋቸው እንቅልፍ ይዟቸው ጥርግ ይላል፡፡

ልብ እንበል እነዚህ ሰዎች አውቆ እንደተኛ ሰው የተጨፈኑት አይኖቻቸው ህብረተሰቡን የሚያገለግሉበት አይናቸው እንጂ ለነሱ ምቾት የሚተጉት አይኖቻቸው ፈፅሞ ለሃያ አራት ሰዓታት አያንቀላፉም፡፡ ትውልዱን እጁን ይዤ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወደ ዕድገት ጎዳና ላሻግረው፣ ይህችን ከተማ ወይም ሀገር ሁለገብ ዕድገት እንዲኖራትና በውስጧ ላሉት ለኑሮ ምቹና የሩቆችን በውበቷና በመልካም መአዛዋ የምትስብ ከተማ ለመፍጠር ወዘተ. የሚሉና ልብን የሚያሞቁ እጅን በጭብጨባ የሚያቀልጡ የመድረክ ላይ ዲስኩሮች የተወሩባቸው ፈጣን አንደበቶች ምን እንደዘጋቸው ሳይታወቅ አንዳንዴ በዓላትንና እንዳንድ ኩነቶችን ተንተርሰው ካልሆነ በቀር በሚያስፈራ ዝምታ ተውጠው ያ መጀመሪያ ላይ ያሰሙን ድምፃቸው ትዝታ ሁኖን አልፎ አልፎ ከሩቅ ይሰማናል እንጂ እነሱማ ‹‹ጊዜዬ›› ነው በምትል የወንበር ላይ ፉክክር ጊዜያችንን ሰርቀው ጊዜያቸውን እየኖሩት ነው፡፡

ታዲያ ልማቱም፣ ምቹና ውብ ከተማውም፣ ከሩቁ ሌሎችን በውበትና በግርማዋ የምትጣራ ከተማም ትቅርና ለኛ የተሰረቀ ጊዜን ከፋይ ማን ይሆን? ያባከነውን የዕድገት ጉጉት በነበረበት የሚመልስልንስ? በነገራችን ላይ ቃላቸውን የበሉት ባለወንበሮች ጉዳይ ሁሉንም ወንበርተኞች የሚመለከት አይደልም፡፡ ለምን ቢባል ጥቂትም ቢሆኑ በተሰጣቸው ጊዜና ወንበር በቻሉት አቅም ለህብረተሰቡና ለተሰጣቸው አደራ ከልባቸው የሚተጉም አሉና ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ስልጣን ላይ በወጡ ማግስት የገቡትን ቃል ከማክበር አንፃር የአስተዳደሩ ገቢ አስተዳደሩን በተፈለገው ልክ ማሳደግ እንዳይቻል ውሱን ቢያደርግም የአስተዳደሩ አመራሮች ባለቻቸው ጥሪት የቻሉትን ያህል ጎንበስ ቀና ሲሉ እያየን ነው፡፡ ቁብነገሩ እኔ የቱ ጋር ነኝ ብሎ እራስን መፈለጉ ላይ ነው ልቡንና ማስተዋሉን ከመለሰልን፡፡

አንዱ ጠቋሚ ጣት ወደ ሌላው ሲያሳይ ቀሪዎቹ ጣቶች ወደኛው እንደሚጠቁሙ ብዙ ጊዜ እንደምንዘነጋ አስባለሁ፡፡ ስለሌሎች ባወራንበት አንደበታቸን ስለኛም ስንፍና አሊያም ባለእዳነት ማውራቱ ተገቢ ነው ሚዛናዊነት እንደሚሷት ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ እናም በነጠላ ከራስ ጋርም መወቃቀስ መልካም ነው፡፡ ታዲያላችሁ በግል ህይወታችንም በርካታ ብክነቶችና ክስረቶች ይታያሉ፡፡ በተለይ ‹‹ሀገሬ ምን አደረገችልኝ?›› እንጂ ‹‹እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት?›› ብሎ መጠየቅ እምብዛም ልምዱ ላላደረገ ማህበረሰብ በበርካታ ነገሮች እራስን ተጠያቂ ማድረግም በዚሁ ልክ አልተለመደም፡፡

ለምሳሌ የተሰጠንን ዕድሜ እንደየ ቅደም ተከተሉ ስንቶቻችን በአግባቡ ተጠቅመንበትና ሌሎችንም ጠቅመንበት ይሆን? እንዴ! አንዳንዱ እኮ አቶ ቤት ገብቶ እንኳን በቤተሰቡ ጀርባ ላይ ተንጠልጥሎ ጡጦ አቃብሉኝ የማለት ያክል የጡረተኛ እናትና አባቱን የጡረታ ብር የሚካፈል በየቤቱ አይጠፋም፡፡ ደሞም በእርግጠኝነት አለ፡፡ ፈጣሪ በአደራ የሰጠውን ዕድሜና ቢሸረፍና ቢሠራበት ከራስ አልፎ ለትውልድ የሚተርፍ መክሊት ተሸክሞ የወጣትነት ጉልበቱን በመንደር ውስጥ ያባክናል፡፡ በሉዋ ለዚህስ ለባከነ ዕድሜ እና ጉልበት ከፋይ ማን ይሆን?

ምናልባት እንዲህ ያሉ ሰዎችን ቀረብ ብላችሁ ‹‹ስማን እንጂ ለምንድነው የሆነ ነገር የማትሠራው?›› ብላችሁ ብትጠይቋቸው ‹‹እንዴ ምን ሥራ አለና? እስቲ ምን ይታይካል? ሁሉም ነገር ፀጥ ረጭ ብሎ የት ሄደን ምን እንሥራ? የሥራ ዕድል ባልተመቻቸበት ምን ልሥራ?›› ብሎ መልሶ እርሶን ይጠይቆታል፡፡ እውነት ነው ነገሮች በሚፈለገው ልክ አልተመቻቹ ይሆናል፣ ለወጣቱ እንደሚገባው በየችሎታው አንዲሠራ በበቂ ሁኔታ የሥራ መስኮች የሉ ይሆናል፣ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ዝቅተኛ መሆን፣ የበረቱ ቁርጠኛ አመራሮች አለመኖር ወዘተ. እጥረት ገጥሞንም ይሆናል፡፡

ነገር ግን ዐይኖቻችንን ከኛ ማን ወሰደብን? ወደ ውስጣችን እንዳያዩስ ማን ጋረደብን? ዙሪያችንን የሚሠሩ ሥራዎችን እንድንንቅና እራሳችንን ከፍ አድርገን ሰቅለን ለማውረድ እንድንቸገር ማን ጋበዘን፣ የስንፍናና ሥራን የመናቅ ግብዣንስ እንድንቀበል ማን አስተማረን? የዚህ ሁሉ ጥያቄ ምላሽ ያለው ማን ዘንድ ይሆን? ብዙ ሠርተን ጥቂት የምናርፍበትን ውድ የወጣትነት ዕድሜያችንን ጡረተኛ አድርገን የጡረተኛ እናትና አባቶቻችንን ያረጀ ወዝ እንድንበላ ማንስ መክሮን ይሆን? ላባከነውና ለማይመለሰው የወጣትነት ጉልበታም ዕድሜያችን በከንቱ ለመባከኑ ተጠያቂው ማነው?

ብዙ ጊዜ ለተደረገ መልካም ነገር እኔም አለሁበት ብሎ እጁን የሚያወጣ ብዙ ሰው አለ፡፡ በሆነ ስህተት ለተባለሸ ነገር ግን ኃላፊነት የሚወስድ አይደለም በባትሪ በፓውዛ መብራት ተፈልጎም አይገኝም፡፡ ይህ ኃላፊነትን ለመውሰድ ያለብን ጠንካራና ከልጅነት ጀምሮ አብሮን ያደገ ድክመታችን ነው፡፡ አሁንም ለባከኑብን ጊዜያቶቻችን፣ በከንቱ ላለፈ ወጣትነት፣ በአግባቡ ለህብረተሰቡ ጥቅም ላላዋልነው ስልጣን፣ ላባከነው ዕውቀት ወዘተ. ከፋይ ማን ይሆን? ሁላችንም ከራሳችን መክረን መልሱን እንፈልግ፡፡ እኔ አበቃሁ ቸር ሁኑልኝ፡፡

# የዘመኑ . . .

ከገጽ 5 የዞረ

በውጭ ባለሃብቶች ተገንብተው እንግዶችን ተንከባክበው የሚያስተናግዱ ዘመናዊ ሆቴሎች በድሬዳዋ በአንፃራዊነት በየደረጀው እንደሚገኙ ፤ በጥቅሉ ከጅምሩም ትልቅ የነበረችው ድሬዳዋ በአመራሮቿና በህዝቧ ጥረት የወደፊት መድረሻዋን ትልቅ ለማድረግ እየሰራች እንደምትገኝ በፎረሙ በሚገባ አሳይተናል ፡፡ይሄንን ይመስላል፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡- ኢንጅነር ጀማል ከጋዜጣችን ጋር ለነበሮት ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ እንዲሁም በአንባቢያን ስም እጅግ እናመሰግናለን፡፡ የሚጨምሩት ሃሳብ ካለ እድሉን ልስጦትና እንሰነባበት፡፡

ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂም ፡- በቅድሚያ ክቡር ከንቲባችን እና ክቡር ምክትል ከንቲባችን አስፈላጊውን ድጋፍ ሲያደርጉ ስለነበር ላመሰግን እወዳለሁ፡፡በመቀጠል ቀደም ሲል እንደገለፅኩት በፎረሙ ለመሳተፍ የነበረን የዝግጅት ጊዜው አጭር ቢሆንም፤ በሚገባ እራሳችንን ለመግለፅ ችለናል ብለን ያሰብነውን ግብአቶች አሟልተን ወደ ፎረሙ እንድናቀና በተለያዩ ደረጃዎች ተልእኮ ወስደው የተንቀሳቀሱ አመራሮች ብሎም ባለሙያዎች አንዳንድ መስዋትነትን በመክፈል ጭምር ከተማቸውን ከፍ አድርጎ ለማሳየት እስከ ፍጻሜው ላሳዩት ተነሳሽነትና ትጋት ምስጋናን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡በመጨረሻም እናንተንም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡አመሰግናለሁ፡፡

# የኢትዮጵያ . . .

ከገጽ 7 የዞረ

በቅርቡም ይፋ እንደሚደረግ ታውቋል፡፡

የአክሲዮን ሽያጩ ኩባንያው ሥራ በአብዛኛው ከባንክ ሥራ ጋር በጣም የተሳሰረ እንደሆነ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ አብዛኛዎቹ ባንኮች የአክሲዮን ግዥ መፈጸማቸውን ተጠቁሟል፡፡

የአክሲዮን ግዥ የፈጸሙ የውጭ የሚጠብቁት ኩባንያዎችን ማንነት ከመግለጽ ቢቆጠቡም፣ ልምድ ያላቸው የአክሲዮን ገበያ ኩባንያዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የዚህ ኩባንያ ዋነኛ ዓላማ 120 ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የፋይናንስ ተደራሽነትን፣ ቁጠባንና ኢንቨስትመንቱን ማለማመድ ነው፤›› ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ የካፒታል ገበያ ሥርዓት መምጣት በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት መሆኑንም አስረድተዋል፡፡ በተለይ ባንኮች የማይደርሱበትን ሥራ መሥረትና ከውጭም ሆነ ከአገር ውስጥ ካፒታል በማሰባሰቡ ረገድ አማራጭ በመፍጠር ኩባንያው ትልቅ ሥራ ይሠራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

የአገሪቱ ኢኮኖሚ የፋይናንስ ፍላጎትን በተመለከተ በሰጡት ተጨማሪ ማብራሪያ፣ የግል ዘርፉ ብቻ በሚቀጥሉ 10 ዓመታት ቢያንስ እስከ 20 ትሪሊዮን ብር እንደሚፈልግ ገልጸዋል፡፡

በመንግሥት በኩልም በሚቀጥሉት አሥር ዓመት ያስፈልጋል ተብሎ የሚታሰበው ከ10 ትሪሊዮን ብር ያላነሰ በመሆኑ፣ ይህ ከፍተኛ የፋይናንስ ፍላጎት በባንኮች ብድር ብቻ ሊሳካ እንደማይችል ጠቁመዋል፡፡

የፋይናንስ ፍላጎቱ ከፍተኛ ስለመሆኑ በምሳሌነት ባቀረቡት መረጃ በ2015 የሒሳብ ዓመት የኢትዮጵያ ባንኮች ያበደሩትን የገንዘብ መጠን ከ500 ቢሊዮን ብር የማይበልጥ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ ውጪ በቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትና ከሌላ የፋይናንስ ምንጭ የሚገኘው ፋይናንስ ተደማምሮ ዓመታዊ የፋይናንስ ፍሰቱ ከአንድ ትሪሊዮን ብር እንደማይበልጥ ተናግረዋል፡፡

በአክሲዮን ኩባንያው ዕቅድ መሠረት አብዛኛው የፋይናንስ ፍላጎትን በተቻለ መጠን በአገር ውስጥ እንዲሸፈን ማድረግ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አገናኝ አባላት እንዳሉት ሁሉ መዋዕለ ንዋይ ገበያውም አገናኝ አባላት እንደሚኖረው፣ ለዚህም ራሱን የቻለ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት እንደሚዘረጋ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ካፒታል ገበያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ፈቃድ የሚያገኙት ከካፒታ ገበያ ባለሥልጣን ሲሆን፣ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ግን ሙሉ በሙሉ የመንግስት ተቋም ነው፡፡

አሁን የኩባንያው ባለአክሲዮኖች የሆኑ ባንኮች ቁጥር 15 ቢሆንም፣ ባንኮች ባለአክሲዮን ባይሆኑም ከኩባንያው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሠሩ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም አንደኛው የሚሠሩበት መንገድ ቀጥታ የአክሲዮን ኩባንያው ባለቤት በመሆን ትርፍ የሚጋሩበት፣ ሁለተኛው ደግሞ ባንኮቹ እንደ ኢንቨስትመንት ባንክ ሆነው ሲመጡ ደግሞ አገልግሎት ሰጪ ሆነው እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡

ሌላው ደግሞ አክሲዮን ኩባንያው ላይ ኢንቨስትም ባያደርጉ ኢንቨስትንት ባንክ ባይሆኑም ዕለት ዕለት የትሬዠሪ ሥራ ሲሠሩ ከአክሲዮኑ ኩባንያው ጋር መገናኘታቸው እንደማይቀርም ጥላሁን (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

አክሲዮን ሽያጩ በፍላጎት የሚፈጸም በመሆኑ እስካሁን አክሲዮን ከገዙት የፋይናንስ ተቋማት በተጨማሪ ሌሎቹም ወደፊት የአክሲዮን ባለድርሻ ለመሆን የሚችሉበት ዕድል እንዳለ ተገልጿል፡፡

አክሲዮኖችን ያልገዙ የፋይናንስ ተቋማት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ ጥላሁን (ዶ/ር)፣ መሥራች ባለአክሲዮኖቹ በሚያስቀምጡት ዋጋ መሠረት አክሲዮን ገዝተው ሊገቡ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

የውጭ ኩባንያዎች የዚህ አክሲዮን ማኅበር መሥራች አባል ሆነው እንዲገቡ ፍላጎት ያለ በመሆኑ እነሱ እየተጠበቁ መሆኑንም ገልጸዋል ሲል የዘገበው ሪፖርተር ነው፡፡

# የዘመኑ ከተሞች . . .

በዳግማዊ ፍቃዱ









በከተሞች መካከል የሚደረጉ ውድድሮች እና የልምድ ልውውጦች ለከተሞች ፈጣን እድገት ጉልህ ፋይዳ እንዳላቸው ይታመናል። ባለፉት ዓመታት ከተሞች በጋራ ለመሥራት ያግዘናል ያሉትን የከተሞች ፎረም መስርተው ሲሠሩና የልምድ ልውውጥ ሲያደርጉ ከነበረበት ሁኔታም መረዳት የሚቻለው ይህንኑ ነው።

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በ2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ነበር የተጀመረው፡፡ ፎረሙ ለስምንት ጊዜ በተለያዩ ከተሞች ተካሂዷል። ይህ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ሲስተናገድ የነበረ መድረክ፣ ከተሞች የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉም ይታወቃል፡፡የዘንድሮው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በአዲሱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ሶዶ ከተማ ከየካቲት ዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ቀን 2016 ዓ.ም “የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልፅግና” በሚል መሪ ሃሳብ ተካሂዷል፡፡

በዛሬው እትማችን የድሬዳዋ ከተማ ስራ አስኪያጅ የሆኑትን ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂምን እንግዳችን አድርገን የጋበዝናቸው ሲሆን ስለፎረሙ አላማ እንዲሁም ስለ ድሬዳዋ ተሳትፎ ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ

ድሬ ጋዜጣ ፡- የድሬዳዋ ከተማ ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂም ከጋዜጣችን ጋር ቆይታ ለማድረግ ላሳዩን ፍቃደኝነት እጅግ እናመሰግናለን፡፡

ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂም ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡- ስለከተሞች ፎረም ስናወራ ምን ዋና ዋና ፋይዳዎች አሉት ?

ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂም ፡- የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ 1663/2014 መሠረት ከተሰጠው ኃላፊነት አኳያ በዋናነት በከተማ አመራር እና አስተዳደር ጉዳዮች ላይ በትኩረት ይሠራል። በከተሞች የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሚችሉ የወል መሠረተ ልማቶች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ የሳይክል መሄጃ መንገዶች የትኞቹ ከተሞች ቴክኖሎጂን አስቀድሞ በመጠቀም እና ችግሮችን ቀድሞ በማወቅ ወደ ተግባራዊ የግንባታ እንቅስቃሴ ስለመግባታቸውም በፎረሙ ላይ ይፈተሿል፡፡

የከተማ ነዋሪዎች እና ተቋማትን በማቀናጀት በተለይ ከተማውን የሚመራው አካል ከተማውን ለመምራት የሚያስችል አቅም እና እውቀት ሊኖረው ይገባል። ከተሞች እየሰፉ እና እያደጉ እንደመሄዳቸው ሁሉ ፍላጎቶችም በዚያው ልክ እየሰፉ የሚሄድ በመሆኑም በተለመደው አሠራር መራመድ አይቻልም፡፡ለእዚህም በከተሞች አመራር ላይ ትኩረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሠራ ነው። ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆንም እያደገ የመጣውን የከተማ ልማት ፍላጎት መምራት የሚያስችሉ አቅሞች የማሳደግ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

በ9ኛው በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የከተሞች ኤግዚቢሽን፣ ከተማን የማስተዋወቅ፣ ከተማን የማነቃቃት፣ የትኛው ከተማ ምን ላይ ነው ያለው ከተማውን የሚመራው አካል ምን ዓይነት ቁርጠኝነት አለው፤ ምን ግብ አለው፤ ምንስ ማሳካት ይፈልጋል፤ የሚለው በስፋት ታይቷል፡፡

በፎረሙ በተመሳሳይ ደረጃ ያሉ ከተሞች ተወዳድረዋል፡፡ ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችም እንዲሁ ክልሉ ባወጣው ስታንዳርድ መሠረት ተወዳድረዋል፡፡ በዚህም ዜጎችን መሠረት ባደረገ መልኩ የዜጎች የእርካታ ደረጃ ለመለካት ተሞክሯል፡፡ ይሄንን ሙሉ በሙሉ ለመከናወኑ በተግባር ወርዶ ለመለካት ብዙ ውስንነቶች ቢኖሩም በተቻለ መጠን ከተሞች በሚያቀርቡት መረጃ መሰረት ያደረገ ምዘና ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ዋናው ነገር ግን ከተሞች አገልግሎታቸውን የማዘመን፣ በቴክኖሎጂ የማስደገፍ፣ ከሕዝብ ጋር በቅርበት የመሥራት ጥረቶች በመኖራቸው እውቅና መስጠት እንደሆነ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በፎረሙ ላይ በተደጋጋሚ ሲገልጹ እንደነበር ማስታወስ ይቻላል፡፡

የልማት አጋሮች እና ከተማን የሚረዱ፣ ከተማ ውስጥ ሆነው የሥራ እድል የሚፈጥሩ እንዲሁም በተለየ መንገድ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ በፎረሙ እውቅና እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል። ሴሚናሮች፣ የፓናል ውይይቶች እንዲሁም የተለያዩ ሁነቶች ተካሂደዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ሃሳባቸውን አንሸራሽረዋል፡፡ በወቅቱ ከተካሄዱ ፓናል ውይይቶች አንዱ ስማርት ሲቲ በሚል ርእስ ከተሞችን ለማዘመን ትኩረት አድርጎ መስራት የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ፓናል ሲሆን የከተማና መሠረተ ልማት አዲስ ፖሊሲ እያዘጋጀ እንደሚገኝ ተመላክቷል፡፡ ለዚያ የሚሆኑ ግብዓቶች በፎረሙ ተሰባስቧል።

‹‹ከተሞች ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የራሳቸው ሚና አላቸው›› የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልፅግና በሚለው መሪ ቃል የተዘጋጀው ዘጠነኛው ፎረም ከተሞች መዘመን አለባቸው በሚለው ቁርጠኝነት ነው ፤ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ከደቡብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን በወላይታ ሶዶ የተካሄደው ፎረም የተቀናጀ የከተሞች ልማት ላይ ትኩረት አድርጓል።

የልማት አንዱና ትልቁ አቅም መንግሥት እንደመሆኑ ልማትን ከግብ ለማድረስ መንግሥት፣ የልማት አጋሮችንና ነዋሪዎችን በማስተባበር እንደሚሠራም ይታወቃል። የከተሞች ፎረም ዓላማም ለልማት ድርሻ ያላቸው አካላት፣ መንግሥት እና የልማት አጋሮች እንዲሁም የከተማ ነዋሪዎችን እውቀት፣ ሙያ እና ሀብት በማስተባበር የሚከናወን መሆኑን ለማመላከት ነው።ጤናማ የውድድር መንፈስ በከተሞች መካከል እንዲፈጠር ከማድረግ አንፃር የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የጎላ ሚና አለው። ከተማን ከከተማ የማወዳደሩ ጉዳይ ባደጉት ሀገራት ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ከተሞቻቸውን እያሳደገ ነው። የልምድ ልውውጥ የማስፋት አቅሙ ከፍተኛ በመሆኑ ጤናማ የውድድር መንፈስ በከተሞቻችን መካከል እንዲደረግ ፎረሙ አግዟል።

የሀገሪቱ ከተሞች ከተለያዩ ሁኔታዎች ተነስተው የተጀመሩና እየሰፉ የመጡ ናቸው፡፡ አሁን ግን የትኛው አካባቢ ለየትኛው መሠረተ ልማት ይዋል የሚለው በትኩረት የሚሠራበት ይሆናል። ዘጠነኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በከተሞች መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል ነው።

ፎረሙ የከተማ ከንቲባዎች እና አመራሮች የነዋሪዎቻቸውን ችግሮች ለመፍታት በጋራ እንዲመክሩ እድል ይፈጥራል፤ ከንቲባዎች በሚመሯቸው ከተሞች በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በመኖሪያ ቤት ግንባታ እና በመሠረተ ልማት አቅርቦት ባለሀብቱን እና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ እንዲሁም ባለቤት በማድረግ ከተሞች ላይ ውጤት ማምጣትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ከተሞችን ውብ፣ ጽዱ እና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር፣ ድህነት ቅነሳ እና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በትኩረት መስራት የሚገባው የትኩረት መስክ መሆኑ በፎረሙ በነበሩ ውይይቶች በጉልህ ሲገለፁ ከነበሩ ነጥቦች አንዱ ነው። ከዚህም ባለፈ ፎረሙ በከተሞች መካከል የእርስ በእርስ ትብብር እና የተሞክሮ ልውውጥ እንዲኖር አስችሏል፡፡

በከተሞች ለሚታዩ ችግሮች መፍትሄ ለማኖር የተናጠል ሳይሆን የጋራ መፍትሔ ለማምጣትና የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ ያስቻለም ነበር ። ፎረሙ የከተሞች ከፍተኛ አመራሮች ተገናኝተው በወቅታዊ የከተሞች የትኩረት አጀንዳ ላይ ጽሁፍ ቀርቦ እንዲወያዩ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ የተሻለ አሠራር ካላቸው ከተሞች ልምድ የሚለዋወጡበት፣ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችንና ችግሮችን በጋራ መፍትሔ የሚያፈላልጉበት ሁኔታን ከመፍጠር አንፃር ሊኖር የሚገባን አሰራር በፎረሙ ተመላክቷል።

ድሬ ጋዜጣ ፡- ኢንጂነር ስለፎረሙ አጠቃላይ አላማና ፋይዳ እንዲሁም የነበረውን ሂደት በሚገባ እንደገለፁልን ይሰማኛል፤ አመሰግናለው፡፡እንደው ቀጥለን እስቲ ‹‹ ድሬዳዋ በ9ኛው የከተሞች ፎረም የነበራትን ተሳትፎ እንዲሁም በምን መንገድ እራሷን ሸጠች ›› ? የሚለውን እንመልከት፡፡

ኢንጂነር ጀማል ኢብራሂም ፡- ድሬዳዋ በ9ኛው የከተሞች ፎረም ንቁ ተሳታፊ ነበረች፡፡ምንም እንኳን የዝግጅት ጊዜው አጭር የነበረ ቢሆንም በሚገባ እራሳችንን ለመግለፅ ችለናል ብለን ያሰብነውን ግብአቶች አሟልተን ነው ወደ ፎረሙ ያቀናነው፡፡

በአገራችን የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት አላዛር ማተሚያ ቤት፡፡የመጀመሪያው ሲሚንቶ ፋብሪካ ኢትዮ ሲምንት የዛሬው ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ፡፡የመጀመሪው ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ፡፡የድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ ዛሬም ድረስ ያሉ የድሬዳዋን የኢንዱስትሪ ፈር ቀዳጅነት የሚመሰክሩ ናቸው፡፡የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር እስካሁን የድሬዳዋ ልዩ መገለጫ መሆኑን አሳይተናል፡፡

አስተዳደሩ ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገት ካለው እምቅ አቅም አኳያ የምስራቁ የኢንዱስትሪ ኮሪደር ለማድረግ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ሁለት አስርት አመታን ያስቆጠረውና አስተዳደሩ በራሱ ወጪ የገነባው የኢንዱስትሪ መንደር በውስጡ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን መያዙን፡፡ኢንዱስትሪ መንደሩ ከጅምሩ ለፋብሪካዎች አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ማለትም መብራትና ውሃን ጨምሮ ሌሎች ግብአቶች እንዲሟሉለት መደረጉ በሂደትም የተጓደሉ መሰረተ ልማቶች በተሻሻለና ዘመኑ በሚጠይቀው መልኩ መሟላታቸው በአምራች ባለሃብቶች ተመራጭ እንዲሆን አስችሎታል፡፡በኢንዱስትሪ መንደሩ ያሉ ፋብሪካዎች በየዘርፉ ለበርካቶች የስራ እድል መፍጠር መቻሉን አሳይተናል፡፡

በአገራችን በፌደራል ደረጃ ተገንብተው ወደ ስራ ከገቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንዱ ነው፡፡ፓርኩ በ2013 ዓ.ም በክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አብይ አህመድ በይፋ ተመርቋል፡፡በአገራችን የመጀሪያው ነፃ የንግድ ቀጠና ድሬደዋ ላይ ተመስርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ ደረቅ ወደብም በድሬዳዋ እንደሚገኝ ለታዳሚው አሳይተናል፡፡

ድሬዳዋ ቀድሞውኑ በፕላን ከተመሰረቱ የአገራችን ከተሞች አንዷ ነች፡፡ በአሁኑ ጊዜም የከተማ ፕላንና አከታተም ብሎም የከተማ መሬትና የካዳስተር ስርዓት ዘመናዊ በሆነና ያሉ ችግሮችን በሚፈታ መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝ ፤በከተማ የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮግራም ድሬዳዋ በርካታ ዜጎቿን ተጠቃሚ ያደረገና ከድህነት መውጣት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የሥራ እድል መፍጠር የቻሉ ታታሪዎች መፍራት መቻላቸውን አሳይተናል፡፡

ድሬዳዋ ለመኖሪያነትና ለስራ ምቹ እንደመሆኗ በርካታ ዜጎች በየአመቱ ይከትሙባታል፡፡በዛውም ልክ የቤት ፍላጎትም እያደገ መጥቷል ምንም እንኳን አመርቂ ነው ባይባልም የነዋሪውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ እንደሚገኙ ፤የከተማ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፤መሰረተ ልማት አሰራር ስርአት ማሻሻያ እና ቅንጅት እንዲሁም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች በድሬዳዋ ያለማቋረጥ እድገት የሚታይበት ዘርፍ መሆኑን አሳውቀናል፡፡

አንድ ከተማ በራሱ ቆሞ መሄድ የሚችለው ገቢውን ማሳደግ ሲችል እንደመሆኑ የከተማ አመራር፣ ፋይናንስና አገልግሎት አሰጣጥ ሥራዎች ልዩ ትኩረት ተሰቶባቸው የሚከናወኑ ስራዎች መሆናቸውን ፤ የቱሪዝም ሃብት የድሬዳዋ ሌላው መገለጫ ነው፡፡በርካታ ሊለሙ የሚችሉ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መዳረሻዎች በድሬዳዋ ይገኛሉ፡፡የጥንቱ ሰው መኖሪያ ዋሻ ለገ ኦዳ ዋሻ ፣ጥናታዊው ከተማ ሃርላ፣የባሊያን ማህበረሰብ እሬሳ ማቃጠያ ፣አፍሪካን ሰሜንተሪ መካነ መቃብር፣ የአሊቢራ ፓርክ፣የቀፊራ ክፍት የገበያ ስፍራ፣ አንፊ ማርኬት... ከድሬደዋ እምቅ የቱሪዝም መስህቦች ውስጥ የሚጠቀሱ እንደሆኑ በፎረሙ ላይ አሳውቀናል፡፡

የተለያዩ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ኮንፍረንሶች በድሬዳዋ በስፋት እንደመካሄዱ ሁሉ በአገር ውስጥና

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተሰጠ ማሳሰቢያ

በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በአስተዳደሩ አገልግሎት የሚሰጡ የግል ፣ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከአፀደ ህፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አገልግሎት የሚሠጡት በስታንዳርድ መሠረት ተገምግመው የዕውቅና ፍቃድ የተሠጣቸው ትምህርት ቤቶች በክፍል ደረጃና የሚገኙበት አካባቢ ከዚህ በታች በዝርዝር የተገለፀ ሲሆን ህብረተሰቡ ፍቃድ ባላቸው የትምህርት ተቋማትን ብቻ ልጆቹን እንዲያስተምር ቢሮው እያሳሰበ በሂደት ላይ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማት እስከ ሰኔ 30/2016 ዓ.ም ተገምግመው ውጤት ሲታወቅ ማስተማር የሚችሉትን በዝርዝር የምንገልፅ መሆኑ እናሳውቃለን፡፡

**በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዕውቅና ፍቃድ ያላቸው ት/ቤት ዝርዝር በክፍል ደረጃና በቀበሌ**

| የት/ቤቱ ስም | የተፈቀደለት የት/ት ደረጃ | አድራሻ | ይዞታ |
|---|---|---|---|
| ጌቴሴማኔ | ከአፀደህፃናት - መጀመሪያ ደረጃ | 01 | የገዳም |
| ጃን ቁ.2 | አፀደህፃናት | 01 | የግል |
| ተውሒድ | ከአፀደህፃናት- ሁለተኛ ደረጃ | 01 | የህዝብ ት/ቤት |
| **02 ቀበሌ** | | | |
| ጀሩሳሌም | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| የሳ/ደ/ኃ/ቅ/ገብሬል | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የቤተክርስቲያን |
| ቅ/ትሬዛ | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል (ሳሊያን ቅርንጫፍ) |
| ሉቀማን ቁ.1 | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የህዝብ |
| ናታን | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ራሔል | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ድሬ ቤተል ቁ.1 | አፀደህፃናት | 02 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| ድሬ ቤተል ቁ.2 | ከአፀደህፃናት - ሁለተኛ ደረጃ | 02 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| ድሬ ቤተል ቁ.3 | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 02 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| ድሬ ቤተል ቁ.4 | አፀደህፃናት | 02 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| አዲስ ራዕይ | አፀደህፃናት | 02 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| ጂቱ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ኤክስለንስ አካዳሚ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ማደም ኤልሣ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| 3MA | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል (ጀርባ ቅርንጫፍ) |
| እናት | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ኤሊጂቤተናታን | ከአፀደህፃናት - ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| ኒል | ከአፀደህፃናት - መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ድሬኢሊትስ | መጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| አቡነ ጎርጎሪዎስ | ከአፀደህፃናት - መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |

**በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዕውቅና ፍቃድ ያላቸው ትቤት ዝርዝር በክፍል ደረጃ**

| የት/ቤቱ ስም | የተፈቀደለት የት/ት ደረጃ | አድራሻ | ይዞታ |
|---|---|---|---|
| **06 ቀበሌ** | | | |
| ጃን ቁ.1 | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 06 | የግል |
| **07 ቀበሌ** | | | |
| ኢሊፍ | አፀደህፃናት | 07 | የግል |
| ጃን ቁ.3 | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 07 | የግል |
| ጃግአልኑር | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 07 | የግል |
| አልፋላሀ | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 07 | የህዝብ |
| አባድር ቁ.1 | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 07 | የህዝብ |
| **08 ቀበሌ** | | | |
| ኢማን | አፀደህፃናት | 08 | የግል |
| ዲንቦራ | አፀደህፃናት | 08 | የግል |
| አባድር ቁ.2 | አፀደህፃናት | 08 | የህዝብ |
| ማያ | አፀደህፃናት | 08 | የግል |
| ቢላል | ከአፀደህፃናት --ሁለተኛ ደረጃ | 08 | የግል |
| አልመርከዝ አልእስላም | ከአፀደህፃናት --ሁለተኛ ደረጃ | 08 | የህዝብ |
| ጡዩር አልጀና | አፀደህፃናት | 08 | የግል |
| አመል | አፀደህፃናት | 08 | የግል |
| አባያዚድ | መጀመሪያ ደረጃ | 08 | የህዝብ |
| አልረሻድ | መጀመሪያ ደረጃ | 08 | የህዝብ |
| ማህደርኑር | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 08 | የህዝብ |
| **09 ቀበሌ** | | | |
| ቅ/ኡራኤል | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የቤተክርስቲያን |
| ፍኖተ ጥበብ | አፀደህፃናት | 09 | የግል |
| ሞቴሽ | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 09 | የግል |
| አልኢኽላስ | አፀደህፃናት | 09 | የመስኪድ |
| ሉቁማን ቁ.2 | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የግል |
| ሉቁማን ቁ.3 | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የግል |

**በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዕውቅና ፍቃድ ያላቸው ትቤት ዝርዝር በክፍል ደረጃ**

| የት/ቤቱ ስም | የተፈቀደለት የት/ት ደረጃ | አድራሻ | ይዞታ |
|---|---|---|---|
| ሻራክሻሊ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ዜድኢ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ዳሩልኡሉም | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የህዝብ |
| የሱፍ አዎኔየን | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| ፈጅር | አፀደህፃናት | 02 | ኃ/ተ/ግ/ማ |
| ፐሮክሲማ | ከአፀደህፃናት - ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| **03 ቀበሌ** | | | |
| አቡነድሪያስ | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 03 | የካቶሊክ ቤተክርስቲያን |
| ቅ/ማርያም ካቴድራል | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 03 | የቤተክርቲያን |
| እመቤታችን | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 03 | የካቶሊክ ቤተክርስቲያን |
| ቁባ | አፀደህፃናት | 03 | የግል |
| ፍኖተ ምስራቅ | አፀደህፃናት | 03 | ባ/የግ/ኃ/የተ/የግ/ማ |
| ብስራተ ገብሬኤል | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 03 | የካቶሊክ ቤተክርስቲያን |
| ድሬአስታር | አፀደህፃናት | 03 | የግል |
| ስክሰስ | ከአፀደህፃናት - መጀመሪያ ደረጃ | 03 | የግል |
| ቅድስት ትሬዛ | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 03 | የግል (ዲፖ ቅርንጫፍ) |
| **04 ቀበሌ** | | | |
| አዲስህይወት | ከአፀደህፃናት -ሁለተኛ ደረጃ | 04 | ኃ/የተ/የግ/ማ |
| እውን ሞዴል | አፀደህፃናት | 04 | የግል |
| ጥላሁን | አፀደህፃናት | 04 | የግል |
| ራኪብ | አፀደህፃናት | 04 | የግል |
| **05 ቀበሌ** | | | |
| የነገብሩህ ተስፋ | አፀደህፃናት | 05 | የግል |
| ኡርጂ | አፀደህፃናት | 05 | የግል |
| ደ/ሠ/መድሃንያለም | መጀመሪያና- መካከለኛ ደረጃ | 05 | የቤተክርስቲያን |

**በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዕውቅና ፍቃድ ያላቸው ትቤት ዝርዝር በክፍል ደረጃ**

| የት/ቤቱ ስም | የተፈቀደለት የት/ት ደረጃ | አድራሻ | ይዞታ |
|---|---|---|---|
| **09 ቀበሌ** | | | |
| ቤተፋሚሊ | አፀደህፃናት | 09 | የግል |
| አልዲያ አልሰላም | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የግል |
| አልፍርቃን | መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የግል |
| **የት/ቤቱ ስም** | **የተፈቀደለት የት/ት ደረጃ** | **አድራሻ** | **ይዞታ** |
| **ቀበሌ ሦስት (3) ኪሎ** | | | |
| ሱሪያ | አፀደህፃናት | 3ኪሎ | የግል |

**የዕውቅና ፍቃድ ጠይቀው ሒደት ላይ የሚገኙ ት/ቤቶች**

| የት/ቤቱ ስም | የክፍል ደረጃ | የሚገኝበት ቀበሌ | ይዞታ |
|---|---|---|---|
| ደሎታ ቁቤ | አፀደህፃናት | 3ኪሎ | የግል |
| መልቲ ወሊ | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| አልኢማን | ከአፀደህፃናት -መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ቤክዋን | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| ድሬኤሊትስ | አፀደህፃናት እና ሁለተኛ ደረጃ | 02 | የግል |
| ጡዩር አልጀና | መጀመሪያ ደረጃ | 08 | የግል |
| ጡዩር አልጀና | አፀደህፃናት | 02 | የግል |
| 3MA | አፀደህፃናት | 02 | የግል (ጎሮ ቅርንጫፍ) |
| ማደምአልሣ | መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ዋሃድአንያ | መጀመሪያ ደረጃ | 09 | የህዝብ |
| እውን ሞዴል | መጀመሪያ ደረጃ | 04 | የግል |
| ማያ | መጀመሪያ ደረጃ | 08 | የግል |
| ዜድኢ | መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ራኪብ | መጀመሪያ ደረጃ | 04 | የግል |
| ፈጅር | መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ራሔል | መጀመሪያ ደረጃ | 02 | የግል |
| ሱሪያ | መጀመሪያ ደረጃ | 3ኪሎ | የግል |

**መግለጫ**

- አፀደህፃናት ማለት ከ4-6 ዓመት የሆኑ ህፃናት የሚማሩበት የክፍል ደረጃ ነው፡፡
- የመጀመሪያ ደረጃ ማለት ከ1-6ኛ የክፍል ደረጃ ነው፡፡
- መጀመሪያና እና መካከለኛ ማለት ከ1-8ኛ ክፍል ሲሆን
- ሁለተኛ ደረጃ ማለት ከ9-12ኛ የሚማሩበት የክፍል ደረጃ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

- በሂደት ላይ ያሉ ትምህርት ቤቶች እስከ ሰኔ 30 ድረስ ተገምግመው ደረጃቸው ሲገለፅ የእውቅና ፍቃድ በተፈቀደላቸው ደረጃ ብቻ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

# የኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋይ ገበያ ከሚያስፈልገው ካፒታል ውስጥ 90 በመቶውን ሰበሰበ

- እስካሁን 15 ባንኮች የመዋዕለ ንዋይ ገበያው ባለድርሻ ሆነዋል

የኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋይ ገበያ አክሲዮን ማኅበርን ለማቋቋምና ከሚያስፈልገው አንድ ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነውን ካፒታል ማሰባሰብ መቻሉን ገለጸ፡፡

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋይ ገበያ ላይ የ50 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ግዥ መፈጸሙን አስመልክቶ በተደረገው የፊርማ ሥርዓት ላይ እንደተገለጸው፣ እስካሁን ኩባንያው ለማሰባሰብ ካቀደው አንድ ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ900 ሚሊዮን ብር በላይ ማሰባሰብ ችሏል፡፡

የአክሲዮን ኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጥላሁን ካሳሁን (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ አሁን የታየው የአክሲዮን ሽያጩ አፈጻጸም የአክሲዮን ሽያጩ የማጠናቀቂያ ጊዜ ነው ተብሎ ከተቀመጠው ማርች 29 ቀን 2024 በፊት አክሲዮን ኩባንያውን ለመሥራት የሚያስችለው ካፒታል ይሟላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከማርች በፊት ይህንን አክሲዮን የገዙት የግል ዘርፉ ኩባንያዎች ቁጥርም ከ25 በላይ መድረሱንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህ ውስጥ የ50 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ከገዛው ግሎባል ባንክ ኢትዮጵን ጨምሮ እስካሁን ወደ 15 የሚሆኑ ባንኮች አክሲዮኖችን የገዙ ስለመሆናቸው ታውቋል፡፡ ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ የገዛው የ50 ሚሊዮን ብር አክሲዮን በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋይ ገበያ አክሲዮን ኩባንያ ውስጥ የአምስት በመቶ ባለቤት ድርሻ እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ ላይ ያለ መሆኑን የገለጹት የግሎባል




ባንክ ኢትዮጵያ የኮርፖሬት ስትራቴጂ ትራንስፎርሜሽን አሲስታንስ ቺፍ ኦፊሰር ወ/ሮ መዓዛ ወንድሙ ለዚህ ማሳያ የሚሆነውን ለውጭ ባንኮች ገበያው መከፈት አንዱ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ እንደ ካፒታል ገበያ መፈጠርና የመሳሰሉ ተግባራት የፋይናንስ ዘርፉን ወደ አዲስ ምዕራፍ እያሸጋገረው ስለሆነ ባንካቸው ይህንን ለውጥ ተከትሎ በተፈጠሩት አዳዲስ አሠራሮ ላይ ተሳትፎውን ለማጉላት ከESX ጋር አብሮ ለመሥራትና የኩባንው ባለድርሻ ለመሆን ውሳኔ በማሳለፍ የ50 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ሊገዛ መቻሉን ገልጸዋል፡

በካፒታ ገበያ ውስጥ እንዲህ ባለው ሁኔታ ተሳታፊ መሆናቸው እንደ አገር ያለወን ጠቀሜታ በማሰብ ጭምር መሆኑን ያስረዱት ምክትል ሥራ አስፈጻሚ በዚህ ኢንስትመንት ውስጥ መሳተፍ ለባንካቸውም ሆነ ለአገር ጠቃሚ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

ኩባንያውን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ካፒታል ለማሟላት ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ የቆየ ሲሆን፣ እስካሁን ያሰባሰበው የካፒታል መጠንም አክሲዮን ኩባንያውን ለማቋቋምና ኩባንያውን ሥራ ለማስጀመር አስፈላጊ የሆነ የቴክሎጂ ግዥዎችን ለመፈጸም ያስችላል ተብሏል፡፡ አክሲዮን ኩባንያው እስከ መስከረም 2017 ዓ.ም. በይፋ ሥራ ይጀምራል ተብሎ እንደሚጠበቅም ከዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

«ገበያውን ለማደራጀት መጀመሪያ የሚያስፈልገው ካፒልትና የሰው ኃይል ነው፤» ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ የገበያው መመርያዎችና ውሎች ቀደም ተብሎ ሲሠራ የቆየ በመሆኑ ከምሥረታው በኋላ ሥራውን ለመጀመር የማይከበድ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡ ሌላው ኩባንያውን ሥራ ለማስጀመር ከወዲሁ ዝግጅት እየተደረገበት ያለው ጉዳይ የቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ይህንን ቴክኖሎጂ ለመግዛት ጨረታ ወጥቶ በሒደት ላይ እንደሚገኝና

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በአነስተኛ የአምራች ዘርፎች የተሰማሩ አንቀሳቃሾችን መደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያግዝ ተገለፀ

በአስተዳደሩ በአነስተኛኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ የሳሙና ምርት ላይ ለተሰማሩ አንቀሳቃሾችን የምርትና ምርታማነትን አቅም ለመጨመር የሚያስችል ስልጠና እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በትላልቅ ደረጃ የሚጠቀሱ ግዙፍ የማኒፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት በቅድሚያ ለአነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በቂ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ቻይናና ህንድን ጨምሮ በአለም ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ያላቸውን አገራት ተሞክሮ ያሳየናል፡፡

እነዚህ አገራት ለአነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጭምር ለምርት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እንዲያቀርቡ የሚያስችል የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡



በድሬዳዋ እንደ አገር ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት መሰረት በማድረግ የተለያዩ የድጋፍና ክትትል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በአስተዳደሩ ላሉ 14 የሳሙና አምራች አነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እየተሰጠ የሚገኘው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በዘርፉ ከሚከናወኑ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አንዱ ነው፡፡

ስልጠናው የስራ ክህሎትን በማሳደግ ምርታማነትን ለመጨመር የሚረዳ እንደሆነ የስልጠናው ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር፤የገበያ መዳረሻን በማስፋት ተወዳዳሪነትንና ትርፋማነትን ከፍ ማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችን የተመለከቱ ሃሳቦች በስልጠናው ተካተዋል፡፡

**በዳግማዊ ፍቃዱ**

# ከ22.2 ሚሊየን ብር በላይ ካፒታል ያለው "አለ ቀሎ የንግድና ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ አክስዮን ማህበር በድሬዳዋ ተመሰረተ

በንግድና ኢንቨስትመንት ስራዎች ውስጥ በመሳተፍ በአገር ዕድገት ላይ የድርሻውን ለማበርከት አላማ ያለው የአለ ቀሎ የንግድና የኢንቨስትመንት አክስዮን ማህበር ተመሠረተ ።

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ የተከበሩ ከድር ጁሃር በምስረታው ስነ-ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር መንግስት ሁሉም ሰው በማህበር ተደራጅተው በአገር ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ የድርሻቸውን ለማበርከት የሚያደርጉት ጥረት እንድምያበረታታ ገልፀው፤ አለ ቀሎ ማህበር ከዚህ በፊት በውጪ አገር ቢደራጁም በአገራቸውም ባላቸዉ ሀብት በንግድና ኢንቨስትመንት ስራ ላይ በመሳተፍ ከእራሳቸው አልፈው ወገኖቻቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት አስተዳደሩ እንደሚያበረታታ ገልፀዋል።

የብልፅግና ፓርቲ ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኃላፊ አቶ ኢብራሂም ዩሱፍ በበኩላቸው አገራዊ የለውጥ ሂደቱን ተከትሎ እንደ አገርና እንደ ድሬዳዋ ባለሃብቶች በሚፈልጉት የስራ ዘርፍ ተሰማርተው ውጤታማ ስራ



እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታዎች እንደተፈጠረ ገልፀው፤ አክስዮን ማህበሩ በአካባቢው ፤ በአገሪቱና በተለያዩ የውጭ አገራት የሚገኙ አባላቶቹን በማሰባሰብ በድሬዳዋና በአገር ደረጃ የተሻሉ ስራዎች ለመስራት የሰነቀው አላማ እንዲሳካ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት መዋቅርና አመራር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደረግ ተናግረዋል ።

አለ ቀሎ የምለው ለስያሜው ተጠቀምን እንጂ ሁሉም ሰው ሼሩን በመግዛት የማህበሩ አባል መሆን ይችላል ያሉት የማህበሩ ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ሀረር መህመድ ማህበሩ በውጭ አገር በሳኡዲ አረቢያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መቋቋሙንና የወገኖቻቸውን በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሲሳተፉ እንደነበረ ጠቅሰው፤ ይህንን ማህበር ወደ አለ ቀሎ ንግድና ኢንቨስትመንት አክስዮን ማህበር በማሳደግ በልማትና በንግድ ተግባራት ላይ ለመንቀሳቀስ ስምምነት በመፍጠር ወደ ተግባር መሸጋገራቸውንም አብራርተዋል ።

የማህበሩ ዋና ስራአስኪያጅ አቶ መሀመድ ፋራህ በበኩላቸው ማህበሩ ከ22.2 ሚሊዮን ብር በላይ ተቋቁመው ወደ ስራ እንደገባና በአገሪቱ በተፈጠረው ለውጥና ሰላም እንዲሁም ምቹ የስራ ሁኔታን በመጠቀም ወገኖቻችንም ተጠቃሚ ለማድረግ ነው ብሏል።

በዕለቱ የድሬዳዋ አስተዳደር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ፣ ነዋሪዎች ፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች ፣ አባገዳዎች፣ ሃደስንቄ ና ታዋቂ ግለሰቦችና የተለያዩ ባንኮች ተጠሪዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ ሆነዋል።

**በኤልያስ አሜ**

**ፎቶ ፡ሙሉአለም ደሴ**

# አድዋ የአፍሪካዊያን "ሰው" የመሆን ማረጋገጫ

በዘመድ ቢሆነኝ

"ከእናቴ ጋር ወደ መዝናኛ ቦታ እየሄድን ሳለ በአካባቢያችን የሚገኙ ነጮች እኔን በድንጋጤ ያዩኝ ነበር፡፡ የነጮቹ ልጆች ደሞ እኔን በመፍራት ወላጆቻቸው ስር ይደበቁ ነበር፡፡ ይህንን ባየሁበት ቀን ከእናቴ ጋር ወደ ቤት ስንመለስ ቤት እንደገባን ሮጬ መኝታ ቤቴ ወዳለው መስታወት ነበር የሄድኩት፡፡ ሌሎቹን እንዲህ ያስደነገጠውን ፊቴን ለማየት!" ብሎ ነበር በአንድ ወቅት በሰጠው ቃለመጠይቅ ላይ ፤ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ፡፡

ይህ አይነቱ የስነ ልቦና ጨለማ የወደቀው በኦባማ ላይ ብቻ ሳይሆን በሚሊየን በሚቆጠሩ አፍሮ አሜሪካዊያን ጥቁር ህፃናት ላይ ጭምር ነው፡፡ በነጮቹ እንደ ኑሮ መርህ ሲወሰድ የነበረው የቀለም መድሎ በአሜሪካ ውስጥም ሆነ በአውሮፓ ውስጥ ብዙ ጠባሳዎችን ትቶ አልፏል፡፡

የማግለያ አይነታቸው በጣም በርካታ ነበር፡፡ ካፌ እና ሬስቶራንት መለየት በጣም ምርጡን ለራሳቸው መጠቀሚያነት በማድረግ ጥቁሮች የሚገለገሉበትን ደሞ በጣም የወረደ ደረጃ ያለው እንዲሆን በመተው ፤ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ነጮችን ከጥቁሮች እና ከሌሎች ነጭ ካልሆኑ ዘሮች በመለየት እና ለለዩት ክፍልም "የተሻለ" የሚል ማዕረግ በመስጠት እንዲሁም የሌሎቹን ያልተሻሉ እና ምግባራቸው ጥሩ ያልሆነ የሚል ስም በመለጠፍ ሁሉ የዘር ኩራታቸውን በተግባር ይገልጡ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በትልልቅ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለምርምር የሚውሉት አይጦች ሳይቀሩ "ነጭ" ናቸው፡፡ ነጩ አይጥ ከጥቁሩ የሚለየው በቆዳ ቀለሙ ብቻ ነው፡፡ ሳይንቲስቶች አይጥን ለምርምርነት የሚጠቀሙት አእምሮአዊ አሰራሩ ከሰው አእምሯዊ አሰራር ጋር በጣም ይቀራረባል ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ እዚህ ላይም ነጮቹ የዘር ኩራታቸውን ገልጠውበታል፡፡

በነሱ አረዳድ ነጩ አይጥ በጣም ለሰው የቀረበ ማሰብ የሚችል ሲሆን ጥቁሩ አይጥ ግን ማሰብ የማይችል ተራ አይጥ ነው፡፡ ነጭ አይጥን ብቻ ለምርምርነት የመጠቀም ምክንያት ዘረኝነት ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡ ፈረንጆች የራሳቸውን ዘር ከፍ አድርጎ ሌላውን ዝቅ ለማድረግ አሁንም ድረስ ሁሉንም መንገዶች በመጠቀም ላይ ናቸው፡፡

በታላቁ HOLLY WOOD የፊልም መንደር በኩል የሚወጡ ፊልሞችን እንመልከት፡፡ በርካታ ፊልሞች ላይ ጥቁር ተዋናዮች ሆን ተብሎ መጥፎ ገፀባህሪያት እንዲጫወቱ በማድረግ በፊልም ተመልካቹ አእምሮ ላይ ጥቁር ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የተያያዘ ተደርጎ እንዲሳሉ ያደርጋሉ፡፡ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በብዛት የሚገቡት ጥቁሮች ሲሆኑ ወደ ማረሚያ ቤቱ ይገባሉ እንጂ አይወጡም፡፡ የማረሚያ ቤቶቹ አያያዝ በጣም አስቀያሚ ከመሆኑ የተነሳ በአጋጣሚ ከእስር ቤቶቹ የሚወጡ ጥቁሮች ቢኖሩ እንኳ ወይ ራሳቸውን ያጠፋሉ ወይ ደሞ በባሰ ወንጀል ውስጥ ይገኙና ተይዘው ወደ እስር ቤቱ ይመለሳሉ፡፡

የነጮቹ ቆዳ ቀለምን መሰረት ያደረገው ግፋቸው ከራሳቸው ምድር አልፎ አፍሪካ ምድር ላይም ሰፍቶ እንደነበር ማናችንም አንረሳውም፡፡ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ አፓርታይድ የሚባል ስርአት ዘርግተው ሀገሬውን በገዛ ሀገሩ እና መሬቱ ላይ ወደ ሁለተኛ ወይም ካሉት ሌሎች ዝርያዎች ወደ የመጨረሻ ዜጋነት አውርደውት ነበር፡፡ በምስራቅ አፍሪካም ሆነ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ነጮች የዘር ብትራቸውን አሳርፈዋል፡፡

የሀሳቤ መነሻ በርግጥም የዘር መድሎን ብሶት ለማተት አይደለም፡፡ያ ሁሉ ራስን ከፍ ሌላው ዝቅ የማድረግ ጥረት "እኛ የሰው ዘር ሌላው ግን እንስሳ "የሚል አድምታ ያለው ሩጫ ለምን አስፈለገ ? የሚል ጥያቄ ለማንሳት እና መልሱን ብዙም ውስብስብ ባልሆነ ታሪካዊ ምሳሌ ለማተት ነው፡፡ ነጮች ይህን አይነት ስልጣኔያቸውን የማይመጥን አስተሳሰብ ለምን ሊያቀነቅኑ ቻሉ? እንዴት እንዲህ አይነት ኢ-ተፈጥሯዊ የሆነ አመለካከት ይዘው ወደ ስልጣኔ መጡ ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡

አንድ ነገር ላይ ኢ-ፍትሀዊ የሆነ ነገር ለማድረግ ስታስብ በመጀመሪያ የህሊና እና የህግ ድጋፍ ለማግኘት ነገሮችን ማመቻቸት አለብህ፡፡ ከድርጊቱ በፊት ድርጊቱ የሚመዘንበትን ሚዛን ማበጀት ይኖርብሀል ፡፡ አንዴ ሚዛኑ ከተሰራ በኋላ ድርጊቶችን እየተከተልክ መጥፎ ነው ጥሩ እያልክ በክርክር ማረጋገጥ አይጠበቅብህም፡፡ ስለዚህ ፈረንጆቹ አፍሪካዊያንን በየትኛውም የዓለም ጥግ ላይ ለቅኝ ገዥነት እና ለብዝበዛ ሲጪቸው መጀመሪያ የሚበዘበዘው አካል ተበዝባዥ ለመሆን የሰውነት ክብሩን አጥቶ ወደ እንስሳነት ዝቅ ማለት እንደሚኖርበት አሰቡ ፤ ከህሊና እና ከሰብዓዊ መብት ጥያቄ ነፃ ለመሆን ጥቁሮችን እንደሰው ሳይሆን እንደእንስሳ ተቀበሉ፡፡ ይሄኔ እነሱን በሰንሰለት አስሮ እንደከብት ለመንዳት ቻሉ፡፡

በአፍሪካ ምድር የታየው የሀብት ምዝበራ መንደርደሪያው የሰውነት ክብርን መንጠቅ ነው፡፡ አንዴ የሆነ ፍጡር እንስሳ መሆኑ ተቀባይነት ካገኘ ሀብት የሌለው ፥ የነፃነት ጥያቄ የማያነሳ ፥ ልክ እንደነጮቹ ሁሉ ለሰው የሚስፈልገው መሰረታዊ ነገሮች ሁሉ የሚያስፈልጉት ዱር ቤቱ የሆነ ይሆናል፡፡ ታዲያ በዚህ ደረጃ ያለን ፍጡር ሀገሩን ብትወርበት ፥ ሀብቱን በጉልበት ብትወስድበት ፥ ጉልበቱን ብትበዘብዝበት ከምን አንፃር ልክ ላትሆን ትችላለህ ? የህሊና ፀፀት የህግም ተጠያቂነት አይኖርብህም፡፡ ስለዚህ ከምን ተነስተው 'ልክ አይደለንም' ይበሉ? ከድርጊቱ አስቀድሞ ሚዛኑን ማዘጋጀት ማለት እንግዲህ ይህ ነው፡፡

በተፈጥሮ ሀብት እንደ አፍሪካ ምድር ያልበለፀገውን መሬታቸው ለመደጎም ሲሉ ፥ ወደ አፍሪካ ምድር ማማተራቸው ግድ ነው፡፡ የስልጣኔያቸው መሰረት ለማቆም አፍሪካን እና አፍሪካዊያንን መጠቀም እንዳለባቸው ያሰቡት ከራሳቸው ባዶ ተነስተውም ነው፡፡ ከላይ እንዳነሳሁት ድርጊቱ የሚመዘንበት ሚዛን ቀድመው ስለሰሩ አፍሪካዊያንን እንደ እንስሳ የሚቆጥር አእምሮ ቀድመው ስላበጁ አሁን ቀጥታ ሄደው ቢወሩ ይችላሉ፡፡ ባሪያ አድርገው ቢሸጧቸው መብት አላቸው፡፡ ስለዚህ የቅኝ ገዥ ዙሪያ ጥምጥሙ ፤ በየመስኩ የራሳቸውን የበላይነት የገነቡት እና በየትውልዱ ስነ ልቦና ውስጥ የጥቁርን የበታችነት የአፍሪካን ሀብት ለመመዝበር ህዝቧንም ለባርነት ለመማገድ ነው፡፡

የአድዋ ድልን ከድንበር ሉአላዊነት ጋር አያይዞ መተንተን የተለመደ ነው፡፡ ድሉ አነሠ በዛ የሚለው ጭቅጭቅ ከዚህ መሠረት ይፈልቃል፡፡ በኔ ግምት የአድዋ ድል ትልቅ ጭብጥ «የሰውነት ክብር» ይሰኛል፡፡ ቀደምቶቻችን ወደ አድዋ የጋለቡት በግፍ የተነጠቁትን የሰውነት መታወቂያ ለማስመለስ ነው፡፡ እንዲያውም ሰው መሆናቸውን በማያዳግም መንገድ ያረጋገጡት አድዋ ላይ ነው፡፡

ወገኖቼ!! ሰው መሆንን ማረጋገጥ ቀላል ነገር አይምሰላችሁ፡፡ አባቶቻችን ከአውሮፓውያን ጋር የሚጋሩትን ግን ደግሞ ከአውሮፓውያን ቀድመው የሚያውቁትን ቅዱስ መጽሐፍ ጠቅሰው ሁላችንም ያዳም ልጆች ነን ይሉ ነበር፡፡ እና ያዳም ልጆች ነን ብለው የሚያምኑ ፈረንጆች ቢቸገሩ የሚደርሱላቸው፣ ቢጠቁ የሚታደጓቸው ወንድሞቻቸው እንደሆኑ ያስቡ ነበር፡፡ በርግጥም የሃይማኖት አንድነት የቀለም ልዩነትን ደምስሶ አዳማዊ ወንድማማችነትን ያስገኘበት የዘመን ምዕራፍ ነበር፡፡ ክርስቶፈር ደጋማ የተባለ የፖርቹጋል ነፍጠኛ ለኢትዮጵያ ደሙን ያፈሰሰው የማተብ አንድነት ስለገፋፋው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባንድ ወቅት የሚያገለግል የኑሮ ዋስትና በሌላው ዘመን አያገለግልም፡፡

ሁላችንም ያዳም ልጆች ነን የሚለው የዝምድና ውል ከእለታት አንድ ቀን ያገለግሎት ዘመኑ አለቀ፡፡ በ1548 ተወልዶ በ1600 እንደጧፍ የተቃጠለው ዦርዳኖ ቡርኖ የተባለ የጣልያን መናፍቅ «ኢትዮጵያውያን ያዳም ልጆች አይደሉም፤ ቅድመ- አዳማዊያን ናቸው እንጂ» ብሎ ፃፈ፡፡ በቡርኖ ዘመን ኢትዮጵያ የጥቁር ዘር ሁሉ የወል ስሙ ነው፡፡ ቅድመ አዳማዊ ማለት ደሞ በአዳምነት ማዕረግ ያልደረሠ ጅምር ፍጡር ማለት ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ጥቁሮች በእግዚር አምሳል የተፈጠሩ አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል፡፡ ያለማለዘቢያ ለመግለፅ፣ ጥቁሮች ከእንስሣትና ከእፅዋት ይመደባሉ ማለት ነው፡፡ ነገሩ ይበልጥ የሚያስገርመን ይህንን አመለካከት ከጥንታዊያን ግሪኮች ነባይ አመለካከት ጋር ስናመዛዝነው ነው፡፡ ጥንታውያኑ ግሪኮች ጥቁሮችን ከአማልክት ጋር ያወዳድሯቸው እንደነበር ለመገንዘብ የሆመርን ውዳሴ መስማት ይበቃል፡፡

ሆመር እንዲህ ይዘምራል፡፡

"እናንት ኢትዮጵያውያን

ከሰው ዘሮች ሁሉ እንከን የሌላችሁ

ከተንኮል ከክፋት ከሰው ድክመት ሁሉ ነፃ የሆናችሁ

ከቶ ከምን ይሆን የተፈጠራችሁ?

ምንድነው ባህሪያችሁ?

እግዜሮች ትሆኑ ወይስ ሰዎች ናችሁ?"

(ከህዲስ አለማየሁ ትርጉም የተጠቀሰ)

ታዲያ በጥንታዊ ግሪኮች ሰው ናቸው አማልክት? ተብለው የተጠረጠሩ ጥቁሮች፣ በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሰው ናቸው እንስሳ? ተብለው ለምን ተጠረጠሩ? የጥቁሮችን ሰውነት መካድ ለምን አስፈለገ? መልሱ ብዙም የተወሳሰበ አይደለም፡፡ የቅኝ ግዛት ዳርዳርታው ለቅኝ የታጩ ህዝቦችን የሰውነት መታወቂያ መንጠቅ ነው፡ ሰው በድንግል ተፈጥሮው መሠሉን ለማጥፋት ልቡና እጁ በቀላሉ አይታዘዙለትም፡፡ ይህንን ለማድረግ ባፍራሽ ንድፈ ሀሳብ መታገዝ ይኖርብታል፡፡

ሰው፣ በጎች ነፍስ የላቸውም ብሎ ራሱን ካሳመነ ጀምሮ በጎችን ወደ ቀይወጥ ለመለወጥ የህሊና ወቀሳ የለበትም፡፡ አውሮፓዊውም ጥቁሮችን ጨፍጭፎ አገራቸውን ለመቀማት ከሰው ተራ አውጥቶ ከዋርካና በጥድ ተራ ማሰለፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ባድዋ ድባቅ የተመታው የጣልያን ቅኝ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያውያኑን ከማይገባቸው ማሣ ላይ የተሰማሩ ገበሬዎች አድርጎ ሳይቆጥራቸው አልቀረም፡፡ የጣልያኑ ጄኔራል (ባሪያቴሪ መሰለኝ) በጦርነቱ ዋዜማ «...ምኒልክን በቀፎ አስገብቼ አበረክትላችኋለሁ» ብሎ ለሮማውያን ወንድሞቹ መጕረሩ በአእምሮው ውስጥ የነበረው ምስል ምን እንደነበር ፍንጭ ይሰጠናል፡፡

«መትረየስ ጠመዱ አሉ በርከክ በርከክ አውሬ መስያቸው ከሰው መወለዴን ማን በነገራቸው?»

አለ አቅራሪ፡፡

ታዲያ አባቶቻችን እንዲህ በአደባባይ የተነጠቁትን የሰውነት ክብር ለማስመለስ ከፍልሚያ ውጭ ምን አማራጭ ነበራቸው?? ፓትሪክ ሄነሪ የተባለው የአሜሪካ አርበኛ «ነፃነቴን ወይም ሞቴን ወዲህ በሉ!» ብሎ በአሜሪካ ተራራዎች ላይ ከመጮኹ አንድ መቶ አመት አስቀድሞ ኢትዮጵያውያን ‹ይኄይስ መዊት በክብር እምሐይው በኃሣር (በውርደት ከመኖር በክብር መሞት ይሻላል) የሚለውን መፈክር ያውቁት ነበር፡፡ (የሰርፀ ድንግልን ዜና መዋዕል ተመልከት)

አባቶቻችን አይን ያጠፋውን አይኑን በለው የሚለው ኦሪታዊ ሕግ ለአድዋ ዋዜማ ተስማሚ ሆኖ አግኝተውታል፡፡ እንደ ሰው ያልቆጠራቸውን ጠላት እንደ ሰው ሊቆጥሩት አልፈለጉም፡፡ አፄ ምኒልክ በጦርነት አዋጃቸው «...እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ፣ የሰውን መድከም አይቼ ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር» አሉ፡፡ በዚህ ንግግር ውስጥ ያለው ትልቅ ነገር ጣልያኑ እንደ ፍልፈል መታየቱ ነው፡፡ አጤ ምኒልክ ያገራቸው ወታደር ለወራሪው ሰብዓዊ ዝምድና ተሰምቶት እንዲሳሳለት አልፈለጉም፡፡ በጦርነቱ ወቅት በተመሳሳይ መልኩ ወራሪን ወደ አውሬ የመለወጥ የስነ ልቦና ቅኝት የነበረ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ በመቀሌ ጦርነት ዋዜማ ራስ አሉላ በተገኙበት ጉባኤ ቀኛዝማች በሻህ ጣልያኑን በዜግነት ስሙ መጥራት ሳያስፈልጋቸው «...በሾተል እየቀነጠስን በግንቡ ውስጥ እንደ አይጥ እንፈጀዋለን» ሲሉ መስማቱን በጅሮንድ ተክለሐዋርያት በግለ-ታሪኩ ይዘግባል፡፡ ታሪክ በሠፈሩት ቁና ይሠፍራል፡፡

ጣልያኖች ከሰው ተራ ወጥተው በፍልፈልና በአይጥ ሰልፍ ውስጥ ገብተው ለእልቂት ተመቻቹ፡፡ አዎ፣ ውርደት እንደ ተሰቦ ነው፡፡ ወደ አዋራጁም ይጋባል፡፡ ወታደር ባለመሆኔ የጦርነቱን ውሎ ማተት አያምርብኝም ፡፡ ያም ሆኖ የአድዋ ድል ዛሬ ብርቅ በሆኑብን ሁለት እሴቶች ረድኤት የተገኘ ይመስለኛል፡፡

እነሂህ ሁለት እሴቶች መተባበርና መደማመጥ ናቸው፡ ፡ ጣልያኖቹ በጊዜው ወደ ጦርነት ሲገቡ ተስፋቸውን የጣሉት በመድፍና በጠመንጃቸው ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ዝነኛ በነበሩበት የውስጥ መቆራቆስ ላይ ነው፡፡ የትግራይ ቅልጥም ሲመታ ሸዋ ያነክሳል ብለው አላሰቡም፡፡ በርግጥም በክፍለ ሀገሮች ውስጥ የተለያዩ ሽኩቻዎች ነበሩ፡፡ እኒህን ሽኩቻዎች አስረስቶ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ለአንድ አላማ ማሠለፍ ምኒልክነትን ይጠይቃል፡፡

. . . እኒህን ሽኩቻዎች አስረስቶ

ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ለአንድ አላማ ማሠለፍ

ምኒልክነትን ይጠይቃል!

መደማመጥ ያልሁትን ላሳይ፡፡ አባ ዳኘው ከዛሬው የይስሙላ ፓርላማችን በተሻለ ሁኔታ ለልዩነቶች ቦታ የሚሰጥ ተንቀሳቃሽ ምክር ቤት በጦርነቱ ወቅት መፍጠር ችለዋል፡፡ ፀሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ በውጊያው ዋዜማ የነበረውን ሁኔታ እንዲህ ይገልፁታል.....

«አፄ ሚኒልክም በበነጋው ሰራዊቱን የቀኙን በቀኝ፣ የግራውን በግራ አሰልፈው ነጋሪትዋን እያስሙቱ ወደሱ ተጓዙ፡፡ ኢጣሊያኖችም ዘበኛው ሲመጣ ባዩ ጊዜ ተመልሰው ወደ እርዳቸው ገብተው ተኙ፡፡ ከዚህ በኋላ ሰራዊቱም እንደ ኤሊ ስንመጣበት ከድንጋይ ይገባል፤ ስንመለስ ይወጣል፤ እንዲህ አርጐ ሊጫወትብን ነውን? ብሎ እጅግ አጥብቆ ተናደደ፡፡ መኳንንቶቹም ተሰብስበው ከዚህ ሰፍረን አድረን በማለዳ እዚያው ካሉበት ከርዱ ድረስ ሄደን እንዋጋለን ብለው መከሩ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም እሺ ብለው ድንኳኑን ለማስመጣት አዘዙ፡፡

ይህ ምክር ካለቀ በኋላ የትግሬው ገዢ ራስ መንገሻ ተሰልፎ በፈረስ ሆኖ መጣ፡፡ እሱም ይህ ምክር እንዳለቀ ባዩ ጊዜ አንድ ነገር ልናገር ይፍቀዱልኝ ብሎ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ እንዲህ አለ፡፡ እንደ ተርታ ነገር ካልሆነ ስፍራ ሄደን ልናስፈጀው ነውን? አለ፡፡ ይህ ምክር የተስማማ ምክር ሆነ፡፡ አፄ ምኒልክም ተመልሰው ከድንኳንዋ ከገቡ በኋላ እንዲህ አሉ፡ ፡ እንግዲህ ከሰፈሬ ወጥቶ ተኩስ አልጀመረ ባይኔ ካላየሁት ተሰልፌ አልወጣም፡፡»

ፀሐፌ ትእዛዝ ያቀረቡትን ዘገባ ወደ ዘመናዊ አማርኛ አሳጥሬ ሳዛውረው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ርዕሰ-ብሔር ምኒልክ ሰራዊታቸውን እየመሩ ወደፊት ሲገሰግሱ የጣልያን ሰራዊት ስልታዊ ማፈግፈግ አድርጎ ወደ ምሽጉ ገባ፡፡ ምኒልክ በቀጣዩ ስትራቴጂ ላይ ለመወያየት አስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ፡፡ በስብሰባው ላይ ወደ ጠላት ምሽግ ሄደን እንዋጋ የሚል ሐሳብ ቀርቦ ባብላጫ ድምፅ ፀደቀ፡፡ ምኒልክም በብዙሃኑ ተሰብሳቢ የቀረበውን ሐሳብ ለማስፈፀም ተዘጋጁ።

ይሁን እንጂ ጄኔራል መንገሻ ዮሐንስ ዘግይቶ ስብሰባውን ከተቀላቀለ በኋላ «ምሽግ ድረስ ሄዶ መዋጋት በወገን ጦር ላይ ጉዳት ያስከትላል» ብሎ መከራከር ጀመረ፡፡ ምኒልክም «እኔ አንዴ ወስኛለሁ፤ ውሳኔዬ ካልጣመህ በሊማሊሞ በኩል ማቋረጥ ትችላለህ» ብለው ሳያሽማቅቁት ሐሳቡ እንዲጤን አደረጉለት፡ ፡ ሐሳቡ በድምፅ ብልጫ ፀደቀ፡፡ በድምፅ ብልጫ ያልሁት «ይህ ምክር የተስማማ ምክር ሆነ» የሚለውን የፅሐፌ ትዕዛዙን አማርኛ ተርጉሜ ነው፡፡ እንደተመለከተው አጤ ምኒልክ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን ለማዳመጥና አወዳድረው የነጠረውን ሐሳብ ለማስፈፀም ዝግጁ ነበሩ፡፡ በአራት ነጥብ የታጠረ ግትርነት አልነበረባቸውም፡፡

እና እላችኋለሁ የሚኒሊክ ፊት ፈላስፋው ሾፐንሀወር እንዳለው ፈካ ያለ ባይሆንም ይህንን በመሰለ የመሪነት ብቃት ነው የየካቲት 23ቱን የአድዋን ጦርነት ድል የነሱት። ሾፐናወርን እንዲህ ላስታውሳችሁና ላብቃ።

ሾፐናወር የተባለ የጀርመን አገር ፈላስፋ ከአድዋ ሠላሳ አምስት አመት አስቀድሞ «ከጥንት ግብፃውያንና ከህንዶች ውጭ ያለው ታላቅ የስልጣኔ ፍሬ ሁሉ በነጮች ጥረት ውጤት ነው፡፡ ከጥቁር ህዝቦች መካከል እንኳ የገዢነትን ስልጣን የሚይዙት በቀለም ፈካ ያሉት ናቸው» ብሎ ነበር፡፡ ያጤ ምኒልክ ፊት ይህንን ንድፈ ሐሳብ በይፋ ለማስተባበል የተፈጠረ አይመስልም?

**አበቃሁ፤ የሳምንት ሰው ይበለን!**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ 09 አሰተዳደር ፅ/ቤት የ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት አላቂ የቢሮ መገልገያ እቃዎችን፤ አላቂ የትምህርት ቤት ዕቃዎች (እስቴሽነሪ) እና የጽዳት እቃዎች መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በዘርፉ የተሰማሩና የሚከተለውን መስፈርት የሚያሚሉ ድርጅቶችን አወዳድሮ ማጫረት ይፈልጋል፡፡

1. በተጠቀሰው የስራ ዘርፍ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር የከፈለ፡፡
2. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገበና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ 5000/ አምስት ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይንም ሲፒኦ ከመወዳደሪያ ዋጋቸውጋር አያይዘውና አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ጨረታው በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሰነዱ ለመግዛት የማይመለስ 200 / ሁለት መቶ ብር/ ሰነዱን በመግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15ቀን የሥራ ቀናት ሰነዱን በቀበሌ 09 ፅ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 13 መግዛት ትችላላችሁ፡፡
6. የጨረታው መከፈቻ በእረፍት ቀን ላይ ከዋለ በቀጣዩ የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡
7. አሸናፊ ተጫራች ሆኖ የሚገኝ ማሸነፉ በተገለጸለት ከግዢ አካል ጋር ውል መፈጸም የሚችል፡፡
8. በውል መፈጸምያ ወቅት 10/100 ውል ማስከበሪያ ማቅረብ የሚችል፡፡
9. ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ህጋዊ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዕለቱ 3፡00 ሰዓት ተከፍቶ 4፡00 ሰዓት ይዘጋል፡፡
10. የጨረታ መከፈቻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘገይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
11. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡-**

**የቀበሌ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት**

**ስልክ ቁጥር 093219027 8እና 0915017361**

## Invitation to Bid

Place and Date: ***Dire Dawa, March, 2024***

Procurement Reference Number: ***DDA/K02AO/PC-001/2016***

1. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** having legal address at:

| | |
|---|---|
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

2. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** now invites sealed bids from eligible and qualified bidders for: ***Construction of Ditch Work (Location: Bargele, Kebele 02)***.
3. Intended Completion Date for the whole of the Works shall be ***150 calendar days***.
4. Bidding will be conducted through **Dire Dawa Competitive Bidding** procedure contained in public proclamation of FDRE and is open to all Eligible bidders.
5. Interested eligible bidders may obtain further information from ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** and inspect the bidding documents at the address given below from 7:30AM – 12:00 PM & 2:00 – 5:30 PM working hours.
6. Qualifications requirements include: Contractors of category ***GC/BC-7 & above*** with license valid for the year ***2016E.C. Work Experience is Required***
7. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non-refundable fee of ***ETB 500*** in ***Cash***.
8. Bidders shall submit their Bids in **two envelopes**, the first envelop labeled as "Technical Proposal and Bid Security" and the second envelope "Financial Proposal", separate sealed and the two envelopes sealed in on other outer envelope.
9. Evaluation is to be carried out in two stages, Technical Proposal first and Financial Proposal of qualified Bidders next.
10. Bids must be delivered to the address below at or *before* ***9:00 AM morning time*** on the ***22nd*** Date from the Date of Announcement. Late bids will be rejected.
11. Bids Will Be Opened In The Presence Of Bidder's Representatives Who Choose To Attend at The Same Date of Submission at ***9:30 AM morning time***
12. All bids must be accompanied by a Bid Security of ***ETB 100,000.00 (One Hundred Thousand Ethiopian Birr) in the form of Cash, an Unconditional Bank Guarantee, or CPO***. The Bid Security shall be valid for 28 days beyond the validity of the Bid.
13. The public body reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to Bidders.
14. The address referred to above is:

| | |
|---|---|
| Public Body: | Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office |
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

## ጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ግዥና የፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በ2016 በጀት ዓመት ከመንግስት በተመደበ በጀት ኮምፒውተር ኮር አይ ፋይፍ (CORE I5 ) እንዲሁም ቪዲዮ ካሜራ (LCD projector klR BÞNtR ) በግልጽ በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም፡-

1. በዘርፉ የተሠማሩና ሕጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው እና በመንግስት የእቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ እንዲሁም የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
3. የዘመኑን ግብር የከፈሉና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው፣
4. ተጫራቾች ለተወዳደሩበት ጨረታ አግባብነት ያለው የተሟላ ማስረጃና ሠነድ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣
5. ተጫራቾች የጨረታ ሠነዱን የጨረታ ማስታወቂያው በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጋቢት12ቀን 2016ዓ.ም ድረስ አየር ላይ የውላል
6. የጨረታ ሠነዱን ብር 200 በመክፈል ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 201 ቀርበው በመውሰድ አስፈላጊውን ዋጋ በግልጽ ቫትን ያካተተ መሆን አለመሆኑን በመግለጽ ሞልተው ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዋናውና ኮፒውን በአግባቡ አሽገው ማስገባት ይችላሉ፣
7. የጨረታ ሳጥን መጋቢት12 ቀን 2016ዓ.ም ጠዋት 4፡00 ሠዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ዕለት 4.30 ላይ ተጫራቶች ወይም ሕጋዊ ወኪላቸው በተገኙበት በዳይሬክቶሬቱ ቢሮ በግልጽ ይከፈታል፣
8. ተጫራቶች ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) የጨረታ ማስከበሪያ በጥሬ ገንዘብ ወይም በሲፒኦ ከጨረታ ሠነዱ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
9. መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ተጨማሪ ማብራሪያና መረጃ ቢያስፈልግ በሚከተለው አድራሻ መጠቀም ይችላሉ፡-

**ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት**

**የስልክ ቁጥር 0915732312**

**ፋክስ ቁጥር 0251-11-77-29**

**ድሬዳዋ**

## ለሶስተኛ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ፑል ለፅዳትና ውበት ኤጀንሲ አገልግሎት የሚውል የደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ አጓጉዞ የማስወገድ አገልግሎት የሚሰጥ የመኪና ኪራይ ጨረታ ማወዳደር ይፈልጋል፡፡


በመሆኑም ተቋማት ለ2016 በጀት ዓመት ለስራ የሚያገለግሉ የፅዳት እቃዎች ግዥዎች በዘርፉ የተሰማሩ አቅራቢዎ በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ጨረታውን መወዳደር ለሚፈልጉ ተሳታፊዎች የጨረታ መስፈርት፡-

1. በዘርፉ የተሰማሩ የንግድ ፈቃድ ያለው
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ
3. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TON NO) ያለው
4. የቫት ተመዝጋቢ ስርተፊኬት ማቅረብ የሚችል
5. የአቅራቢነት ሠርተፊኬት ማቅረብ የሚችል
6. የጨረታ ማስከበሪያ 10,000 (አስር ሺህ ብር) ወይም CPO ወይም በጥሬ ማስያዝ የሚችል ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ መግዛት ይኖርበታል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን 300,00 (ሶስት መቶ ብር) ከተማ ስራ አስኪያጅ 1ኛ ፎቅ ፋ/ግ/ዳይሮክትሬት ክፍል መግዛት ይችላሉ፡፡
8. ጨረታው በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዛኑ ዕለት 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻችሁ በተገኙበት በከተማ ስራ አስኪያጅ በፋይናንስና ግዥ ክፍል ይከፈታል፡፡
9. መ/ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ በአቅራቢነት መሞላት ያለበት ተሞልቶ የተጫራች ፊርማና ማህተም ከሌለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
10. የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዱ ኦርጅናል እና ኮፒ በማድረግ በስም በታሸገ ኢንቨሎፕ መቅረብ አለበት

ማሳሰቢያ፡ መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ የስ/ቁ 09 13 84 54 37 ወይም 09 15 75 53 24**



# የኢትዮጲያና እና የበርበራ ወደብ ጉዳይ

በማቲያስ እንዳለ

በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) እና በሶማሌላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ መካከል በተደረገው የመግባቢያ ስምምነት መሠረት፣ ኢትዮጵያ የበርበራ ወደብን ለመጪዎቹ 50 ዓመታት ለንግድና ለጦር ሠፈርነት እንድትጠቀምበትና በምትኩም ኢትዮጵያ ለሶማሌላንድ ኪራይ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ልትከፍል፣ እንዲሁም ከኪራዩ ታሳቢ የሚሆን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ወይም ከሌላ አትራፊ የንግድ ድርጅት ድርሻ እንዲኖራት ለማድረግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡

ይህንን የመግባቢያ ስምምነት ተከትሎ የሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት ፕሬዚዳንት ተቃውሟቸውን በመግለጻቸው ምክንያት፣ አንዳንድ ዓለም አቀፍና አኅጉራዊ ድርጅቶች ሁኔታው እንደሚያሳስባቸው ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል የአውሮፓ ኅብረት፣ የአፍሪካ ኅብረት፣ ኢጋድና የዓረብ ሊግ ይገኙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በርካታ አገሮች የተፈጠረውን ውጥረት በሰላማዊ መንገድና በንግግር እንዲይይዙት ሐሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጉዳዩ ላይ ሐሳብና አስተያየታቸውን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡

ይህም ከፊሉ መንግሥት የወሰደውን አቋም በመደገፍ ኢትዮጵያ ለህልውናዋ ስትል የወደብ አገልግሎትና የባህር በር ለማግኘት ያደረገችው ስምምነት ስለሆነ ተገቢ ነው ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት ዕውቅና ውጪ የተደረገ በመሆኑ ኢትዮጵያን ዲፕሎማቲክ ውግዘት እያስከተለባት ነው፣ በዚህም ሳቢያ ተነጂ ትሆናለች የሚል የመከራከሪያ ሐሳብ ያቀርባሉ፡፡ የክርክራቸውን ሐሳብ ሲያጠናክሩም ኢትዮጵያ አሁን ላይ ከዲፕሎማሲው ዓለም እየተገለለች ነው፣ የዓለም አቀፍንም ሆነ አኅጉራዊ ሕጎችን በመጣስ የተደረገ ስለሆነ ችግር አለበት በማለት በደምሳሳው ስሜታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በሁለቱ ወገኖች የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ይዘት ሲፈተሽ በዋነኛነት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚሸፍን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም ማለት አንደኛው ኢትዮጵያ የበርበራን ወደብ ለቀጣዮቹ 50 ዓመታት በሊዝ ውል ለመጠቀም የሚያስችል ስምምነት ላይ የደረሱ መሆናቸውን የሚገለጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከበርበራ ወደብ ጋር በተያያዘ 20 ኪሎ ሜትር በሚሸፍን የባህር አካባቢ ላይ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል የሚሠፍርበት ቦታ እንዲኖራት የሚፈቅድ ነው፡፡ በምትኩ ደግሞ ኢትዮጵያ ለወደቡ ከምትከፍለው የ50 ዓመታት ሊዝ ዋጋ ላይ የሚታሰብ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ወይም ከሌላ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ድርሻ እንዲኖራት ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሶማሌላንድ ሉዓላዊ አገር እንድትሆን ዕውቅና ለመስጠት መስማማቷን ይገልጻል፡፡

ይህንንም እውነታ የሶማሌላንድ ፕሬዚዳንት በአዲስ አበባ የመግባቢያ ሰነዱን በፈረሙበት ወቅት ባደረጉት ንግግር በማያሻማ መንገድ ገልጸውታል፡፡ በተቃራኒው የኢትዮጵያ የመንግሥትም ሆነ የፓርቲ ባለሥልጣናትና በመንግሥት የሚደገፉ የመገናኛ ብዙኃንና የዩቱብ ተንታኞች ይዘቱን በማዛባት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ወደብና የባህር ኃይል መሥፈሪያ ቦታ አገኘች በማለት በሰበር ዜና መልክ ሲገልጹት ሰምተናል፡፡ ይሁን እንጂ በሦስተኛው ቀን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ባወጣው መግለጫ የባህር በርና ወደብ የተገኘው በቀይ ባህር ዳርቻ ሳይሆን፣ በኤደን ባህረ ሰላጤ መሆኑን ገልጧል፡፡ ይህም የተሳሳተ አገላለጽና የተጋነነ አቀራረብ አሁን ላይ እያየን ያለውን ውዝግብ አስነሳ፡፡

የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የብልፅግና ደጋፊ የማኅበራዊ ሚዲያ ተንታኞችና የማኅበረሰብ አንቂዎች የተፈረመውን የመግባቢያ ሰነድ ደግፈው ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው፣ እንዲሁም ቋሚ ስምምነት እንደተፈረመ በመቁጠር ሐሳባቸውን ሲገልጹ ይሰማሉ፡፡እነዚህ ወገኖች ሐሳባቸውን የሚያቀርቡት የስምምነት ሰነዱን ትክክለኛ ይዘት በመረዳትና ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ በአግባቡ ተገንዝበው ሳይሆን፣ድጋፍና ባልተጨበጠ ሕልም ላይ ተመሥርተው እንደሆነ ከክርክር አቀራረባቸው ስሜታዊነትና ወገንተኛነት መረዳት ይቻላል፡፡

በተቃራኒው ይህንን የመግባቢያ ስምምነት የሚቃወሙ ወገኖች ደግሞ ይህ ስምምነት ለኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም በአግባቡ ከመመዘን ይልቅ፣ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ብቻ በማጉላት ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ፓርቲያቸውን ለማውገዝ ሲሯሯጡ ይታያሉ፡፡ አስገራሚው ነገር እነዚህ ወገኖች ምናልባትም ከሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት በላይ ለጉዳዩ ትልቅ ቦታ ሰጥተው ሲዘግቡና ትንሹንም ትልቁንም የተቃውሞ መግለጫ በማንሳት በማጋነን ጭምር የኢትዮጵያን መንግሥት ለማጋለጥና ለማውገዝ ሲጠቀሙበት መመልከታችን ነው፡፡

በዚህ ረገድ የአውሮፓ ኅብረት፣ የአፍሪካ ኅብረት፣ ኢጋድና የዓረብ ሊግ ድርጅቶችና ግብፅ፣ አሜሪካ፣ ቱርክና የመሳሰሉት አገሮች ጉዳዩ ያሳስበናል በማለት ያወጡትን የተለሳለሰ መግለጫና አንዳንድ የኬንያ የፓርላማ አባላት የሰጡትን ጠንከር ያለ አስተያየት መሠረት በማድረግ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በጠቅላላው ኢትዮጵያን እንደተቃወመና እንዳስጠነቀቀ አድርገው ሲያቀርቡ ይታያሉ፡፡ አንዳንዶቹ ስምምነቱ የጨረቃ ወደብ ስለሆነ የሚያስገኘው ጥቅም የለም እስከማለትም ደርሰዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች የተቃውሟቸው መነሻ ብልፅግናን መጥላታቸው ይመስለኛል፡፡

ለዚህም እንደ ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ሊያገለግለን የሚችለው ቀደም ሲል በኢሕአዴግ ይመራ የነበረው የኢፌዴሪ መንግሥት የሚያከናውነውን የልማት ሥራ ከመደገፍ ይልቅ፣ የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ አሉታዊ ጎኑን በማጉላት ላይ ጊዜያቸውን ያጠፉ የነበሩ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ግለሰቦች የነበሩ መሆናቸው ነው፡፡ አሁንም ከዚያ ስህተት ተምረን የተፈረመውን የመግባቢያ ሰነድ ይዘት በመፈተሽና ያስነሳውን ተቃውሞና ያስገኘውን ድጋፍ በጥንቃቄ በመፈተሽ ሚዛናዊ ሐሳብ ከማቅረብ ይልቅ፣ በጭፍኑ በመቃወምና በማውገዝ ላይ የተመሠረተ ሐሳብ ማቅረብን የሙጥኝ ብለው እናገኛቸዋለን፡፡

የስምምነቱ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ደጋፊዎች መዘንጋት የሌለባቸው አገሮች ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ የሚወስዷቸው አቋሞች፣ በተለይም በሌላ አገር ላይ ሥጋት የሚፈጥር ከሆነ ከተወሰኑ አካላት ጠንከር ያለ ተቃውሞ ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም፣ በሒደት መልክ መያዙ የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሶማሌላንድ ወቅታዊ ሁኔታን ከሞንቴቪዶ ስምምነት አንፃር በመመልከት የስምምነቱን ሕጋዊነት/ሕገወጥነት መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡

የሞንቴቪዶ ስምምነት እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 26 ቀን 1933 የተፈረመ ሲሆን፣ ሥራ ላይ የዋለው ደግሞ ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ከዲሴምበር 26 ቀን 1934 ዓ.ም. ጀምሮ ነው፡፡ በዚህ ስምምነት አንቀጽ አንድ መሠረት የአንድን አገር ቁመና ለመመዘን ተቀባይነት ያላቸው መሥፈርቶች ተብለው የተቀመጡት በቋሚነት የሚኖር ሕዝብ፣ ዳር ድንበሩ የታወቀ ግዛት፣ የመንግሥት መኖርና ከሌሎች አገሮች ጋር ግንኙነት የመፍጠር አቅም የሚሉት ናቸው፡፡እንዲሁም አንቀጽ ሦስት የአንድ አገር መኖር ከሌሎች አገሮች ዕውቅና መስጠት ጋር የተያያዘ አለመሆኑን በማያሻማ አኳኋን ይገልጻል፡፡ ይኸው አንቀጽ አንዲት አገር ከሌሎች አገሮች ዕውቅና ከማግኘቷ በፊት አንድነቷንና ነፃነቷን የማስከበር፣ብሎም ይጠቅመኛል ያለችውን አደረጃጀት የመፍጠርና ሕግ የማውጣት መብት እንዳላትም ያስቀምጣል፡፡

ሌላው በዚህ ስምምነት ላይ የተቀመጠው ድንጋጌ አንቀጽ ሰባት ሲሆን፣ ዕውቅና በግልጽ ወይም በዝምታ ሊሰጥ እንደሚችል ማስቀመጡ ነው፡፡ በዝምታ በሚሆንበት ጊዜ እያንዳንዱ ድርጊት አዲሱን አገር ዕውቅና ለመስጠት ታስቦ የሚደረግ መሆኑን የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚያም ባሻገር በአንቀጽ 11 ላይ የተቀመጠውን ዝርዝር ሁኔታ ስንመለከት በጦር መሣሪያ በተደገፈ ኃይል ወይም በዲፕሎማቲክ ማስፈራራት ላይ የተመሠረተ ጫና፣አሊያም በማንኛውም ዓይነት አስገዳጅ ዕርምጃ የተደገፈ ስምምነት ከተደረገ ተቀባይነት እንደማይኖረው ያስቀምጣል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን አስገዳጅ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያና ሶማሌላንድ የወደብና የባህር በር አጠቃቀምን አስመልክተው ያደረጉትን የመግባቢያ ስምምነት ስንመረምረው፣ የሶማሌላንድ መሪዎች ወደውና ፈቅደው ያደረጉት ስምምነት ሲሆን፣ በምትኩም ከኢትዮጵያ የሊዝ ኪራይ የሚያገኙበት መሆኑን አረጋግጠው የገቡበት ስምምነት መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ በሶማሌላንድ ላይ የኃይል ዕርምጃም ሆነ ሌላ ዓይነት ሥጋት የሚፈጥር ጫና አሳድራ የገባችበት ስምምነት ሳይሆን፣ የጋራ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል በድርድርና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመግባቢያ ሰነድ ስለተፈራረሙ ሕገወጥ ነው ሊያስብል የሚችል ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ይህ ማለት ግን ምንም እንኳ ሶማሌላንድ ላለፉት 32 ዓመታት ቀደም ሲል የነበረው የሶማሊያ መንግሥት መፍረሱን ተከትሎ ራሷን በራሷ ስታስተዳድር የቆየች ሲሆን፣ የፌዴራል መንግሥት ከተቋቋመ በኋላም ቢሆን የፌዴራል መንግሥቱ አካል ሆና ያልቆየች ብትሆንም፣ የሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት አሁንም ድረስ እንደ ራሱ አካል አድርጎ ስለሚቆጥራትና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የተለያዩ ባለመሆናቸው በድርጊቱ መከፋቱ አይቀርም፡፡ይህንንም መከፋት ደግሞ ከቻለ በኃይል ካልሆነለት ደግሞ በዲፕሎማሲው ዓለም የቻለውን ያህል በመጮህና በማስጮህ ተፅዕኖ ለመፍጠር ጥረት ማድረጉ የሚጠበቅ ነው፡፡ የሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት አሁን እያደረገ ያለው እንቅስቃሴም ይህንኑ እውነታ ያመለክታል፡፡ አስገራሚ የሚሆነው የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን አላስፈላጊ መንፈራገጥ ነው፡፡

ምንጭ፡-ከተለያዩ ማህበራዊ ድህረ ገፆች

## 9ኛው . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ደሞዝ ለመክፈል ፣ የምግብ ማብሰያ ማገዶ እና ንፁህ ውሀ አቅርቦት ይጠይቅ የነበረውን ከፍተኛ ወጪ መሸፈን መቻሉንና ውጤታማ ስራ መሰራቱን የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሀላፊ አቶ ሱልጣን አሊይ ተናግረዋል ።

የትምህርት ቤት ምገባ በተለይም በትምህርት ጥራት ተደራሽነትና የትምህርት ተሳትፎን በማሳደግ ረገድ አስተዋፆው በእጅጉ የጎላ መሆኑን የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ ወ\ሮ አየለች እሸቴ ተናግረው፤ ይህም ፕሮግራም የምግብ ዋስትና ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ወላጆች ከትምህርት ገበታ ውጪ ያሉ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ከማበረታታት ባሻገር ልጆች ወደ ትምህርት ገበታ ከመጡ በኋላም በክፍል ውስጥ በሚማሩት ትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ የሚያስችል በመሆኑ ለትምህርት ጥራት ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ይገኛል ብለዋል ።

**በአለማየሁ አበበ**

**ፎቶ :- በሙሉአለም ደሴ**

## <<በተቋማት . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ለማጠናቀቅ የየተቋማቱ የሪፎርም አስተግባሪ ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት በድሬዳዋ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ገብተው ስራውን እንዲያጠናቅቁ እና በተቋማት የሚታዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ከሰላም እጦት ተለይተው የማይታዩ ብቻ ሳይሆን በዘርፉ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ሌሎች እንደሀገር እየፈተኑን ለሚገኙ ችግሮች ሁሉ መነሻ በመሆናቸው የችግቹን ጥልቀት በዚህ ልክ በመረዳት በዘርፉ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የተጀመረው ሪፎርም የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ የተቋማቱ አመራሮችና ባለሞያዎች የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡም የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሀርቢ ቡህ አቅጣጫ አስቀምጠዋል፡፡

ምንጭ፡ ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ

ፎቶ፡ ሰላም አበበ

## በኢትዮጲያ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በኢንቨስትመንት አማራጮች ላይም የሀገራቱን ባለሀብቶችን ለመሳብ እና በቅርስ እና ጥበቃ ዙሪያ በትብብር ለመሥራት በሚያስችላቸው ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል ።

በተመሳሳይ ዜና አምባሳደሩ በድሬዳዋ አስተዳደር በእንግሊዝ መንግስት ድጋፍ የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን የጎበኙ ሲሆን በንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት (one wash),በጤና፣ በሴፍትኔት፣ በቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ የተሰሩ ተግባራት እንዳስደሰታቸው ገልጸው፤ በተለይም በመጠጥ ውሃ አቅርቦት የለገ-ኦዳ ፕሮጀክትን በመጎብኘት ከዚህ በፊት የነበረውን ድጋፍ በእጥፍ ለማሳደግ እና በይበልጥም በአዳዲስ የልማት እቅዶች ላይ ለመስራትም ቃል ገብተዋል ።

አምባሳደር ዳረን ዌልች በጥንታዊቷ ሀርላ የሚገኘውን ጥንታዊ መካነ ቅርስም የጎበኙ ሲሆን በቅርቡ በአስተዳደሩ ይፋ የሆነው ከ 6 ተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ኪነ-ህንጻ በአርኪዮሎጂስቶች በቁፋሮ መገኘቱን ተከትሎ በጥንታዊቷ የሀርላ መንደር የተገነባውን መኖሪያ ቤቶች ፣ የመቃብር ስፍራዎች ፣ መስጊዶች ፣በዘመኑ የነበሩ የኪነ-ህንጻ ጥበቦችን ተዘዋውረው ተመልክተዋል።

በጉብኝታቸውም በጥንታዊቷ ሀርላ ከተማ የኪነ ህንጻ ጥበቦች፣ እምነት ና ሀይማኖት ጥንተ ስልጣኔ ማሳያ የሆኑ ግኝቶችን በማየታቸው መደነቃቸውን ተናግረዋል፡፡

አምባሳደሩ ዳረን ዌልች በድሬዳዋ አስተዳደር የተደረገላቸውን ደማቅ አቀባበል አድንቀው ኢትዮጵያ የበርካታ ታሪካዊ ቅርሶች እና የጥንታዊ ስልጣኔ መፍለቂያ ትልቅ ሀገር ናት ብለዋል።

ኢትዮጵያ የየራሳቸው ታሪክ፣ቋንቋ፣ ባህልና ልምድ፣ እንዲሁም ከ80 በላይ የሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተስማምተውና ተከባብረው በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነታቸውን ጠብቀው ለዘመናት አብረው የኖሩባትና የሚኖሩባት የመቻቻል ተምሳሌትም መሆኗዋንም አስረድተዋል።

በአስተዳደሩ የጥንታዊ የሀርላ መንደር እና ሌሎች መሰል ቅርሶቿ ለዓለም ለማስተዋወቅ እንዲሁም ጎብዎችን በመሳብ በኩል የጎላ ፋይዳ እንዳላቸውም ነው የተገለጸው።

**በሰላም ለማ**

**ፎቶ፡-ሙሉዓለም ደሴ**

## "ከባለድርሻ አካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር ያለንን አጋርነት አጠናክረን እንቀጥላለን "

ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ

የምስራቅ ሪጂን ኢትዮ -ቴሌኮም ለድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለቢሮ መገልገያ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች ድጋፍ አደረገ።

ከተቋሙ በቀጣይ የድሬዳዋ ፖሊስ ለሚያደርገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ በዝግጅቱ ላይ ተገልጿል ።

በርክክብ ስነ-ስርዓቱ ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የድሬደዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ እንደተናገሩት ሰላም የሁላችንም የኑሮ መሠረት መሆኑን በመገንዘብ ሰላም ለማስጠበቅ ፖሊስ ብቻውን የሚሰራው ስራ አለመሆኑን እና ከአጋር አካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ ለመስራት ከመቼውም ግዜ በላይ ዝግጁ መሆናቸውን የተናገሩት ኮሚሽነር ዓለሙ ከምስራቅ ሪጂን ኢትዮ ቴሌኮም ጋር ያለንን ግንኙነት ሠፊ እና ከዚህ ቀደም የድሬዳዋ ፖሊስ ባከናወናቸው የለውጥ ስራዎች ከተለምዶ አሠራር ተላቆ ወደ ዲጅታል በተደረገው ሽግግር የጥሪ ማዕከልን ከማዘመን አንፃር የምስራቅ ሪጂን ኢትዮ ቴሌኮም ድርሻ እንደነበረው ጠቅሰው፤ በቀጣይ በአስተዳደር ደረጃ ለተያዘው የስማርት ሲቲ ጉዞ ተቋሙ በመንገድ ላይ ለሚተክላቸው ካሜራዎች በጋራ እንደሚሰሩ እና አሁን ላይ ስለተደረገው ድጋፍ በድሬዳዋ ፖሊስ ስም ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።



የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን ለድሬደዋ ፖሊስ ያስረከቡት አቶ ጣሰው ሽመልስ በምስራቅ ሪጂን ኢትዮ ቴሌኮም የኦፕሬሽን ዳይሬክተር በበኩላቸው እንደተናገሩት የድሬዳዋ ፖሊስ እና ኢትዮ ቴሌኮም ምስራቅ ሪጂን በጋራ የሚያከናውኗቸው በርካታ ስራዎች መኖራቸውን ገልፀው፤ ከጥበቃ እስከ ቴክኖሎጂ ሽግግር የተሳሰረ መሆኑን እና ይህን ድጋፍ ሲያደርጉ የመጀመሪያቸው አለመሆኑን የተናገሩት አቶ ጣሰው ሽመልስ ይህን የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ ለመደገፍ ያነሳሳቸው በከተማው የሚገኙ ጣቢያዎች ላይ የተመለከቷቸው የመገልገያ እጥረት መሆኑን እና ይህ ደግሞ እንደተቋም ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር የተፈፀመ ተግባር ሲሆን በቀጣይም በጋራ እንደሚሰሩ ጨምረው ገልፀዋል ።

የምስራቅ ሪጅን ኢትዮ ቴሌኮም ከዚህ ቀደም #620 የጥሪ ማዕከልን በማደራጀት በኩል ትልቅ እገዛ ያደረገ ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ የዋጋ ግምታቸው ከአንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ብር በላይ የሚሆኑ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል ።

## ከ 2 ሚሊዮን ብር በላይ የዋጋ ግምት ያላቸውን የተለያዩ ጌጣጌጦችን ከቤተሰቦቿ ላይ በጓደኛዋ ግፊት ሰርቃ የተሰወረችው ተጠርጣሪ ግለሰብ ፖሊስ ባደረገው ብርቱ ክትትል በቁጥጥር ስር መዋሏ ተገለፀ

የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 9 ሰአት በወረዳ 4 ልዩ ስሙ መብራት ሀይል አዩቤ ጋራዥ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የግል ተበዳዮች ከቤት ውስጥ የስርቆት ወንጀል እንደ ተፈፀመባቸው ለፖሊስ አቤቱታ ማቅረባቸውን ፖሊስ ገልጿል ።

የገንደ ቆሬ ፖሊስ ጣቢያ ወንጀል ምርመራ ክፍል ተወካይ ኃላፊ ዋና ሳጅን ስንዱ ካሳሁን የድርጊቱን አፈፃፀም እንዲህ ስትል ትገልጻለች። ተከሳሿ ግለሰብ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሶስት ጓደኞቿን ከቤተሰቦቻቸው ላይ ያላቸውን ንብረት እንዲዘርፉ በመንገር የዘረፉትንም ንብረት ሸጠው ከተማ ቀይረው የራሳቸውን የተሻለ ህይወት እንደሚኖሩ ታሳምናለች። ታዲያ በንግግሯ የተታለለችው ሌላኛዋ ተከሳሽ ግለሰብ ከቤት እንደደረሰች በሳጥን ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን የዋጋ ግምታቸው ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የወርቅ እና ብር ጌጣጌጥ ሰርቃ በድንገት ወላጅ እናታቸውን በሞት የተነጠቁ ቤተሰቦቿ ከሀዘናቸው ሳይፅናኑ ልብ ሰብራ ወደ ጓደኛዋ ታመራለች። የተሰረቁ ንብረቶቹን የተመለከተችው የወንጀል ድርጊቱን ጠንሳሿ ግለሰብ በመደሰት በፍጥነት ለደላሎች ተናግራ በማሸጥ ወርቁን ሰርቃ ያመጣችው ተከሳሽ ግለሰብ ከሁለት ጓደኞቿ ጋር አያይዛ ወደ ሀረር ከተማ ትልካቸዋለች። ታዲያ ከቀናት በኋላም የስርቆት ወንጀሉ የተፈፀመባቸው ቤተሰቦች ጉዳዩን ለፖሊስ ማድረሳቸውን የሰማችው የወንጀሉ ጠንሳሿ ተከሳሽ አላየሁም አልሰማሁም ስትል ቆይታ የፖሊስ ምርመራ አላፈናፍን ሲላት ለግል ተበዳዮች ተጠርጣሪዎቹ የት እንደሚገኙ እራሷን ታማኝ እና አዛኝ በማስመሰል ትናገራለች ።



ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የገንደ ቆሬ ፖሊስ ጣቢያ የምርመራ ቡድኑን አደራጅቶ ከሀረሪ ፖሊስ ጋር በመነጋገር ባደረገው ብርቱ ክትትል ተጠርጣሪዎችን በሀረር ከተማ ከሚገኘው ጭፈራ ቤት ውስጥ በቁጥጥር ስር አውሎ በተጨማሪም የተለያዩ የምርመራ እና ክትትል ስራዎችን በመስራት ንብረቱን ያሸጡ ደላሎችንም በመያዝ ከተሸጠበት ቦታ ንብረቶቹን ማሰባሰብ መቻሉን ዋና ሳጅን ስንዱ ካሳሁን ተናግረዋል።

ፖሊስ በሰራው ስራ የተደሰቱት የግል ተበዳዩችም በገንደ ቆሬ ፖሊስ ጣቢያ ተገኝተው በአጭር ቀን ውስጥ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር በማዋል የተሰረቀውን ንብረት ፖሊስ ትኩረት ሰጥቶና በድንቅ ሙያዊ ብቃት እንዲመለስ በማስቻሉ የድሬዳዋ ፖሊስ ወንጀልን በመከላከል እና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ በተግባር ማረጋገጥ በመቻላቸው መደሰታቸውን ገልፀው ምስጋናቸውንም አቅርበዋል ።



በአሁኑ ወቅት ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ እያጣራ መሆኑ ታውቋል።

## "አያቶቻችን ደማቸውን አፍሰው ያቆዩትን ሀገር እኛ ደግሞ ደማችንን ለወገናችን በመለገስ እናስቀጥላለን "

ም/ኮማንደር ሻንበል ተካኝ

የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ

የአድዋ ድልን ምክንያት በማድረግ የፅዳት ዘመቻ እና የደም ልገሳ መርሀ ግብር ተከናወነ።

መርሀ ግብሩን ያስተባበሩት የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ እና የሰላም አሽከርካሪዎች ማህበር አመራር እና አባላት በጋራ በመሆን ነው ፡፡

128ኛው የአድዋ ድል በዓልን በማስመልከት የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ እና የሰላም አሽከርካሪዎች ማህበር አመራር እና አባላት በጋራ ባከናወኑት የፅዳት ዘመቻ እና የደም ልገሳ መርሀ ግብር ላይ ተገኝተው መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የትራፊክ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ም/ኮማንደር ይሄነው ሽፈራው እንደተናገሩት ሰላም የአሽከርካሪዎች ማኅበር ህጋዊ ስርዓትን ተከትለው እያከናወኑት የሚገኙት ስራዎች እና ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተለይ ስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ የጠፉ የተገልጋይ ንብረቶችን በታማኝነት በመመለስ በኩል እያከናወኑት ያለው ስራ የሚያስመሰግን ነው ብለዋል፡፡ በቀጣይ ማህበሩን የመደገፍ ስራዎችን አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል ፡፡

የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ም/ኮማንደር ሻንበል ተካኝ በበኩላቸው እንደተናገሩት የአድዋ ድል አያቶቻችን በቀኝ ገዥዎች እጅ ሳይወድቁ አሻፈረኝ በማለት ያስመዘገቡት ድል ለአፍሪካዊያን ትልቅ ኩራት መሆኑን ተናግረው፤ አያቶቻችን ደማቸውን አፍሰው ያቆዩትን ሀገር እነሱ ደግሞ ደማችንን ለወገናችን በመለገስ እና አካባቢያችንን በማፅዳት ተግባር ተሳታፊ በመሆን አርአያነት ያለው ተግባር መፈጸማቸውን ጠቅሰው፤ የሰላም አሽከርካሪዎች ማህበርም ከፖሊስ ጋር በመተባበር ወንጀልን ከመከላከል ባሻገር በተለያዩ የበጎ አድራጎት እና የልማት ስራ ተሳታፊ በመሆናቸው እና በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ለሚያሳዩት አርአያነት ያለው ተግባር አመስግነው በቀጣይ ጣቢያው ከማህበሩ ጎን በመቆም ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡



በኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት ሲንየር ሴኪዩሪቲ ዳይሬክተር የሆኑት ም/ኮማንደር ጉልማ ታዬ በበኩላቸው እንደተናገሩት ከዚህ ቀደም በመልካ ጀብዱ ከምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮች ተቀርፈው የሰላም አሽከርካሪዎች ማህበር በፀጥታ ስራ ላይ የጎላ ተሳትፎ ከማድረግ ባሻገር እያከናወኑት ያሉት ተግባር የሚያስመግን መሆኑን ጠቅሰው፤ የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ማህበሩን ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል ፡፡

የሰላም አሽከርካሪዎች ማኅበር አባላት ለድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የትራፊክ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ም/ኮማንደር ይሄነው ሽፈራው ለማህበራቸው ምስረታ ላደረጉት ድጋፍ ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን በፅዳት ዘመቻው እና የደም ልገሳ መርሀ ግብሩ ላይ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ፣ የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ከፍተኛ አመራሮች እና ቁጥራቸው 70 የሚሆኑ የሰላም አሽከርካሪዎች አባላት ተሳታፊ ሆነዋል።




## ውል መሰረዝ ፤ ማፍረስ እና በስምምነት ማቋረጥ

### ውል_መሰረዝ

ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንደኛው እንደ ውሉ ባለመፈፀሙና የውሉን ግዴታ በመጣሱ በተዋዋዩ ወይም በፍርድ ቤት ውሉን ወይም በውሉ የተቋቋሙትን ግዴታዎች ቀሪ ማድረግ ውል የሚሰረዘው ከመሠረቱ ግድፈት ስላለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የውል መሠረዝ ምክንያት ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታን ከመፈፀምና ካለመፈፀም ጋር ተያይዞ የሚከሠት ነው፡፡ የውል መሠረዝ ሥርዓትም የራሱ የሆነ አካሄድ አለው፡፡ ይኸውም ውሉን የመሠረዝ ፍላጎት ያለውን ወገን የውሉ ግዴታ ባለመፈፀሙ የተነሳ ከህግ ወይም ከውሉ ከራሱ ባገኘው መብት ተጠቅሞ ውሉን ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አጋጣሚም ግዴታው ባለመፈፀሙ የተነሳ የደረሰውን ጉዳት ከማረጋገጥ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ ጥያቄ አቅራቢው ሁልጊዜ ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የውል ይሰረዝልኝና ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በህጉ አግባብ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ. 1784 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ሰ/መ/ቁ. 32299 ቅጽ 8

### ውል ማፍረስ

በህጉ የተቀመጡት የውል አመሰራረት መስፈርቶችን ያላሟላና ግድፈት ያለበት በመሆኑ የተነሳ የውሉ ወይም በውሉ የተቋቋሙትን ግዴታዎች መቅረት ውል ማፍረስና ውል መሠረዝ በውል የተቋቋሙት ግዴታዎች ከሚቀሩባቸው መንገዶች ውስጥ የሚካተቱ ቢሆንም ምክንያታቸውና ውጤታቸው የተለያዩ ነው፡፡ የውል ማፍረስ ከውል አመሠራረት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሲሆን ውሉ ከአመሰራረቱ በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱ ግድፈት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውል መሰረዝ ጉዳይ ከውል አመሰራረት ችግር የሚነሳ ሳይሆን ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታውን ካለመወጣት የሚመነጭ ነው፡፡ ሰ/መ/ቁ. 32299 ቅጽ 8

ውል በስምምነት ማቋረጥ /ቀሪ ማድረግ/

ተዋዋይ ወገኖች በውል አቋቁመውት የነበረውን ግዴታ በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በስምምነት ቀሪ ሲያደርጉ የተለየ ፎርም መከተል እንዳለባቸው የሚደነግግ አስገዳጅ ድንጋጌ የለም፡፡ የውለታ በተዋዋዮች ስምምነት መቋረጥ (terminate) መደረግ ከውል መፍረስ ወይም ከውል መሠረዝ የተለየ ባህሪና ውጤት ያለው መሆኑን አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ውል በስምምነት ቀሪ ማድረግ ውልን ከማሻሻል/ ከመለወጥ እና ውል ከመተካት የተለየ ባህሪ፣ ይዘትና ውጤት ያለው መሆኑን፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1722 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1826 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የውሉ በተዋዋዮቹ ፈቃድና ስምምነት መቋረጥ (ቀሪ) መሆን የተዋዋይ ወገኖች የወደፊት የውል የመፈፀም ግዴታ የሚያስቀር መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የውሉ መቋረጥ /ቀሪ/ መሆን ያለፈውን ሁኔታ የማይነካ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውል ቀሪ መሆን ተዋዋዮቹ በውል አቋቁመውት የነበረውን መብትና ግዴታ ቀሪ የማድረግ ውጤት የሚኖረው መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1807 /ለ/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሰ/መ/ቁ. 63063 ቅጽ 14፣ ፍ/ህ/ቁ. 1682-84፣ 1






# የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ሻምፒዮና በድምቀት ተጠናቋል

በብሩክ ደስታ

የመስቀለኛ እግር ኳስ ቡድን በታሪካቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የዲቪዚዮኑ አሸናፊ ሆነዋል።

በድሬዳዋ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አዘጋጅነት ከህዳር 16ቀን 2016 ዓ/ም እስከ የካቲት 22ቀን 2016ዓ/ም በድሬዳዋ ከተማ በ14 ክለቦች መካከል የተካሄደው የከፍተኛ ዲቪዚዮን ሻምፒዮና በድምቀት ተጠናቋል።

በ ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ በተደረገው ደማቅ ስነ ስርዓት የመስቀለኛ እግር ኳስ ቡድን ከፍተኛ ነጥብ በመሰብሰብ የዲቪዚዮን ዋንጫ እና 200ሺ ብር በመሸለም ባለድል ሆኗል።

ገንደ አብዲቦሩ 2ተኛ ደረጃን በመያዝ የብር ሜዳልያ እና የ150ሺ ብር ሽልማት እንዲሁም ድሬ ካባ 3ኛ ደረጃ በመያዝ የነሐስ ሜዳሊያ 100ሺ ብር የገንዘብ ሽልማት ከፌዴሬሽኑ ተበርክቶላቸዋል።

በዚህ ውድድር የላቀ ስፖርታዊ ጨዋነት ዋንጫ ሐረር ቡና ክለብ ምስጉን ተሸላሚ ሆኗል።

ከመስቀለኛ ክለብ ስንታየሁ አበባው የዓመቱ ኮከብ ተጫዋች ፤ ሞሀባ አሊ ከገንደ አብዲ ቦሩ ክለብ በ13 ጎል የኮከብ ግብ አስቆጣሪ ክብርን አግኝቷል። ስንታየሁ ንጉሴ ከመስቀለኛው ኮከብ ግብ ጠባቂ ፤ ኮከብ አሰልጣኝ



እንስቷ ምስጋና አሰፋ ከመስቀለኛ ክለብ የዋንጫ ተሸላሚ ሆነዋል።

የዕለቱ የክብር እንግዳ የአስተዳደሩ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር በደማቁ የመዝጊያ ስነስርአት ላይ በመገኘት ለአሸናፊዎቹ የዋንጫ እና የገንዘብ ሽልማት አበርክተዋል።

በርካታ ተመልካች የታደመበት ፣እጅግ ደማቅ በሆነው ዝግጅት ላይ አቶ ኢብራሂም ዩሱፍ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የመንግስት ተጠሪ ፣ኮሚሽነር አለሙ መገራ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ እና የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት እንዲሁም የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ፊራንኦል ቡልቻ እና የድሬዳዋ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈፃሚዎች ጨምሮ ሌሎች ተጋባዥ የክብር እንግዶች የሜዳሊያና የፀባይ ዋንጫ ሽልማት ተበርክቷል።

ይህ የድሬዳዋ እግር ኳስ ዋንጫ ከብዙ ዘመናት በኃላ ከአዳዲስ ክስተቶች ጋር ታጅቦ በከተማዋ እግር ኳሱ ላይ መነቃቃትን ፈጥሮ ፤ ከተማሪዎች ማርሽ ባንድ እስከ ደጋፊዎች ህብር ዜማ ፣በርችቶች ያቀጣቀጠው ሜዳ ፍፃሜውን ድምቀት አላብሶት የ2016 ከፍተኛ ዲቪዚዮን ክለቦች ሻምፒዩናው 91 ጨዋታን አስተናግዶ እንደደመቀ ድሬዳዋ ላይ በስኬት ተጠናቋል።

## ድሬዳዋ ስታዲየም በፊፋ የእውቅና ማረጋገጫ ተሰጠው



የድሬዳዋ ስታዲየም ሜዳው በአለም አቀፍ ደረጃ ጨዋታዎችን የማስተናገድ እውቅና ማረጋገጫ ስርተፊኬት አግኝቷል።

የድሬዳዋ ስታዲየም ሰው ሰራሽ ሳር የተነጠፈለትን የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ በፊፋ መስፈርቶችን ደረጃ ማሟላቱን ማረጋገጫ ዕውቅና ሰርተፍኬት ከዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ማህበር ( ፊፋ ) ክቡር የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር ተቀብለዋል ።

የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ/ም በድሬዳዋ ስታዲየም በደማቅ ሁኔታ በተከናወነው ስነስርዓት የሜዳው ሳር ንጣፍ የስራው የታን ኢንጂነሪንግ ባለቤት ፉሀድ ኢብራሂም ከፊፋ የተላከውን የእውቅና ሰርተፍኬት ለአስተዳደሩ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር አበርክቷል።

ክቡር ከንቲባው የተቀበሉትን ሰርተፍኬት ለድሬዳዋ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር ፊራንኦል ቡልቻ አስረክበዋል።

የድሬዳዋ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር ለመላው የስፖርት ቤተሰብ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

ከባለፉት 15 ቀናት በፊት የድሬዳዋ ስታዲየም የሰው ሰራሽ የሳር ንጣፍ በፊፋ ባለሙያዎች መገምገሙ ይታወሳል።

(ምንጭ:የድ/ወ/ስ/ኮሚሽን ይፋዊ ገፅ)

## ድሬዳዋ ከተማ ድል አድርጓል !



የኢትዮጵያ ፕርሚየር ሊግ አስራ ስድስተኛ ሳምንት መርሐ ግብር ድሬዳዋ ከተማ ሀምበሪቾ ዱራሜን 1ለ0 በሆነ ውጤት አሸንፏል።

የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ የመጀመሪያውን ዙር ጨዋታ በአዳማ ከተማ መጠናቀቁን ተከትሎ የሊጉ ሁለተኛ ዙር በድሬዳዋ ከተማ ጅማሮውን ማድረግ ችሏል።

በደጋፊዎቹ ፊት ጨዋታውን ያደረገው ድሬዳዋ ከተማ ከዕረፍት መልስ ዘራይ ገ/ስላሴ ባስቆጠረው ብቸኛ ጎል 1-0 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችለዋል።

በሁለቱ ቡድኖች ጨዋታ ጅማሬ ላይ በነበረው ከባድ ዝናብ ምክንያት ጨዋታው ቢዘገይም ከፊፋ የዕውቅና ማረጋገጫን ያገኘው የድሬዳዋ ኢንተርናሽናል ሜዳ ያለምንም እንከን ጨዋታው ተደርጎበታል።

ድሬዳዋ ጨዋታውን ማሸነፉን ተከትሎ ነጥቡን 22 በማድረስ ደረጃውን ወደ 8ተኛ ከፍ ማድረግ ችሏል።

በአንፃሩ ሀምበሪቾ ዱራሜ በውድድር አመቱ አስራ አንደኛ ሽንፈታቸውን በማስተናገድ በ7 ነጥቦች 16 ተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።

በ17 ተኛ ሳምንት የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ ድሬዳዋ ከተማ ከ ኢትዮጲያ ቡና ጋር እሁድ መጋቢት 1 ምሽት 1:00 ሰአት ላይ በድሬዳዋ ስታዲየም የሚፋለሙ ይሆናል።